## የተጠቂዎች መመሪያ

# ለዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ ጀስትስ ሲስተም

ካውንስል ፎር ኮርት ጀስትስ
Justice for the Community

## ስለ ኦፊስ ኦፍ ቪክቲም ሰርቪስስ ኤንድ ጀስትስ ግራንትስ

የኦፊስ ኦፍ ቪክቲም ሰርቪስስ ኤንድ ጀስትስ ግራንትስ (OVSJG) ቢሮ ተልዕኮ በዲስትሪክ ኮሎምቢያ ውስጥ የሕዝብን ደህንነት የሚጠብቁ ፕሮግራሞችን ማልማት፣ በገንዘብ መደጎም፣ እና ማዋቅር፡ የፍትህን አስተዳደር ማበልጸግ፡ ለወንጀል ተጠቂዎች፣ ለወጣቶች፣ እና ለቤተሰቦቻቸው የእንክብካቤ ስርዓት መፍጠር ነው። ተልዕኮውን ለማሳካት፣ OVSJG ለወንጀል ተጠቂዎች እና ተመላሽ ዜጎች ማህበረሰብ አቀፍ እና ዲስትሪክ ኤጀንሲ አገልግሎቶችን የማዋሃድ እና የገንዘብ ድጎማ ይሰጣል። በተጨማሪም፣ OVSJG በዲስትሪክት የሕዝብ እና የቻርተር ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለውን ከትምህርት ቤት የመቅረት ችግር ለመቀነስ የተነደፉ ጥረቶችን ያስተዳድራል፣ እና የወጣት እስረኞችን የማረም፣ በስልጠና መቅረጽ፣ እና በቡድን የተደራጁ ወጣቶችን የመመለስ ጥረቶችን ይደግፋል። OVSJG የስቴት አስተዳደር ኤጀንሲ ሲሆን ሃላፊነቱም የዲስ የወንጀለኛ ፍትህ ስርዓትን በመምራት ማቀድ፣ ማዋቀር፣ ማስተዳደር፣ ጥናት ማድረግ፣ ማሰልጠን፣ እና ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት ነው። OVSJG በወንጀለኛ ፍትህ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ ተጠቂዎች እና ወንጀለኞች ያላቸውን ሚና፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ አሰራር በመስጠት፣ ጥቃትን ለማቋረጥና ለመከላከል ለሥራ አስፈፃሚው ለፖሊሲ የሚሆኑ የባለሙያ ምክር፣ አስተያየት እና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል።

## ስለ ኮውንስል ኦፍ ኮርት ኤክሰለንስ

የተቋቋመው በዲስትሪክት ኮሎምቢያ ውስጥ በ 1982 ሲሆን፣ የኮውንስል ኦፍ ኮርት ኤክሰለንስ (CCE) በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ሰዎችን በእኩልነት የሚያገለግል እና ጠንካራና በጣም የበለጸጉ ማህበረሰቦችን በመፍጠር ሞዴል የሚሆን የፍትህ ስርዓት ራዕይ ያነገበ ለትርፍ ያልተቋቋመ ከማንኛውም የቡድን ድጋፍ የጸዳ የሲቪክ አስተዳደር ነው።

የ CCE ተልዕኮ ሕዝቡን በእኩልነት ለማገልገል በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ የፍትህ ስርዓቱን ማጎልበት ነው። CCE ጥናቶችን ለማከናወን፣ ፖሊሲ ለማርቀቅ፣ ሕዝቡን ለማስተማር፣ እና የሲቪክ ተሳትፎን ለማሳደግ ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ በመስራት መፍትሔዎችን እያወጣ ለውሳኔ ያቀርባል።

Council for Court Excellence
1111 14th Street NW, Suite 500
Washington, DC 20005-5628
202.785.5917

courtexcellence.org
facebook.com/courtexcellence
twitter.com/CCE_for_DC

Copyright © 2017 Council for Court Excellence. ይሄንን ሰነድ በከፊልም ሆነ ሙሉ ለሙሉ ማባዘት የሚቻለው በፍቃድ ነው። በ victimsguide.courtexcellence.org ላይ በመጎብኘት የዚህን መመሪያ በመስመር (ድረገጽ) ላይ ያግኙ።
ይሄንን መመሪያ እዚህ ላይ ያውርዱ courtexcellence.org/digital-library.
በደብዳቤ እንዲላክልዎ በዚህ ኢሜይል ያድርጉ info@courtexcellence.org.

## ምስጋና

CCE *የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያን ጀስትስ ሲስተም የተጠቂዎች መመሪያን* ለማሻሻል ጊዜአቸውን እና ዕውቀታቸውን ላካፈሉት የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴ አባላት በሙሉ ምስጋናውን ይገልፃል።

## የጋራ ዋና ሰብሳቢዎች

**ጌይል ኤል. ዌስቶቨር** | ኤቨርሼድስ ሳዘርላንድ (ዩኤስ) ኤልኤልፒ*

**ማቲው ራይት** | አርንት ፎክስ ኤልኤልፒ*

## ኮሚቴ

**ኒኪ ቻርልስ** | ኔትወርክ ፎር ቪክትም ሪከቨሪ ኦፍ ዲሲ

**ሳራ ኮኔል** | ኦፊስ ኦፍ ዘ አተርኒ ጀነራል ፎር ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ

**ዳውን ዳልተን** | ዲሲ ኮአሊሽን አጌነስት ዶሜስቲክ ቫዮለንስ

**አውድሪ አይዝማን** | ዲሲ ሴፍ (ሰርቫይቨርስ ኤንድ አድቮኬትስ ፎር ኢምፓወርመንት)

**ታይሪያ ፊልድስ** | ሜትሮፖሊቲያን ፖሊስ ዲፓርትመንት

**ሪቻርድ ቢ. ሆፍማን** | ጀስትስ

ስትራቴጂስ* **ሳምዌል ሲ. ካፐላን** | ቦዬስ

ሺለር ፍሌክስነር ኤልኤልፒ*

**ጌራሊን አር. ላውረንስ** | ላው ኦፍ ጌራሊን አር. ላውረንስ

**ጄኒናይን ማክሌን** | ኦፊስ ኦፍ ዘ አተርኒ ጀነራል ፎር ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ

**ሳራ ማክሊላን** | ኦፊስ ኦፍ ዘ አተርኒ ጀነራል ፎር ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ

**ብሪጂት ስታምፍ** | ኔትወርክ ፎር ቪክትም ሪከቨሪ ኦፍ ዲሲ

*CCE የቦርድ አመራር

ይሄ መመሪያ በኦፊስ ኦፍ ቪክትም ሰርቪስስ ኤንድ ጀስትስ ግራንትስ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በከንቲባው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቢሮ በተሰጠው የገንዘብ ድጋፍ ፈንድ ቀጥር 2017-CCE-01 መሰረት በካውንስል ኦፍ ኦርት ኤክሰለንስ ቢሮ የተዘጋጀ ነው። በዚህ መመሪያ ላይ የቀረቡት አስተያየቶች፣ ውጤቶች፣ እና ድምዳሜዎች ወይም ጥቆማዎች የአቅራቢዎቹ ነው እንጂ የከንቲባውን መደበኛ የሥራ አስፈፃሚ ቢሮ አቋም ወይም ፖሊሲዎችን አያንጸባርቁም።

# ከጋራ ዋና ሰብሳቢዎች የተላከ መልዕክት

ሴፕቴምበር 2017

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የወንጀል ፍትህ አሰጣጥ ሂደት ለወንጀል ተጠቂዎች ፈልጎ ማግኘት በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል፣ እንደዚሁም ተጠቂዎች እነርሱን ለመርዳር የተዘጋጁትን መረጃዎች ለመፈለግ እና ለማግኘት ከአቅም በላይ ሊሆንባቸው ይችላል። በእነዚህ መሰል ችግሮች በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ የወንጀል ተጠቂዎችን ለማገዝ፣ ዘ ካውንስል ፎር ኮርት ኤክሰለንስ (CCE) ለመጀመሪያ ጊዜ በ 1988 *የዲሲ የወንጀል ፍትሕ ስርዓት የተጠቂዎች መመሪያን* አሳትሟል። እስካሁን ድረስ፣ ከ 100,000 ቅጂዎች በላይ *የተጠቂዎች መመሪያ* በመላው ዲሲ ተሰራጭቷል።

ለዲሲ ኦፊስ ኦፍ ቪክቲም ሰርቪስስ ኤንድ ጀስትስ ግራንትስ በቀረበልን የችሮታ የገንዘብ ድጋፍ ምስጋና ይግባውና፣ ይሄንን *የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ጀስትስ ሲስተም የተጠቂዎች መመሪያን* አራተኛ ዕትም ስናቀርብ በደስታ ነው። ይሄ የመመሪያው ዕትም የተሻሻለው እና የጎለበተው በ CCE የቦርድ አመራር አባላት ስትሪንግ ኮሜት እና በየአካባቢ ውስጥ ያሉ የተጠቂዎች አገልግሎት ሠራተኞች እና ባለሙያዎች በኩል ነው። ለእነሱ እና ለሌሎቹ የማህበረሰብ አባላት እና ለበጎፈቃድ ሠራተኞች ለዚህ ፕሮጀክት ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋናችንን ለመስጠት እንወዳለን።

ይሄ መመሪያ የተዘጋጀው ለሕግ ማማከሪያ አገልግሎት ሳይሆን ለመረጃ ዓላማ ብቻ ነው። የዲሲ ተጠቂ እነሱን ላጋጠማቸው የተለየ ችግር ከጠበቃ ጋር ለመማከር የሚፈልጉ ከሆነ፣ የቪክቲም ሌጋል ኔትወርክን በዚህ ስልክ 202-629-1788 ላይ ማግኘት ወይም በድረገጽ vlndc.org ላይ መሄድ አለባቸው። የዲሲ ወንጀል ተጠቂ ላለው ማንኛውም ሌሎች ጥያቄዎች በስልክ ወይም በአጭር የጽሁፍ መልዕክት በ 1-844-4-HELPDC (1-844-443- 5732) ላይ, ወይም የ 24-ሰዓት፣ የፖሊስ ያልሆነ ክፍት መስመር፣ ወይም በመስመር ላይ dcvictim.org በመሄድ ድጋፍ ማግኘት ይቻላል።

ይሄ *የተጠቂዎች መመሪያ* ለዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ስለዚህ መመሪያ ማንኛውም ዓይነት ጥያቄዎች ካላቹህ፣ ወይም ተጨማሪ ቅጂዎችን ለማዘዝ የምትፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ ካውንስል ፎር ኮርት ኤክሰለንስ በዚህ at 202-785-5917 ይደውሉ ወይም ቀጥሎ ባለው አድራሻ ላይ ያግኙ info@courtexcellence.org.

ከአክብሮት ጋር

ጌል ኤል. ዌስቶቨር
*ኤቨርሼድስ ሳዘርላንድ (ዩኤስ) ኤልኤልፒ*

ማቲው ራይት
*አርንት ፎክስ ኤልኤልፒ*

# ማውጫ


ለዲሲ ተጠቂዎች አንገብጋቢ ጉዳዮች ........ 1

የዲሲ የወንጀለኛ ፍትህ አሰጣጥ ዳሰሳ ........ 5

ከችሎት በፊት ያሉ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ሂደት ........ 7

የችሎት ሂደት ........ 11

ከወንጀል ችሎት መዋል በኋላ ........ 17

የዲሲ የፍትሃብሄር የፍትሕ አሳጣጥ ስርዓትን ዳሰሳ ........ 21

የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የካሳ አሰጣጥ ፕሮግራም ........ 25

ለቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች መረጃ ........ 29

ግብአቶች ........ 35

የፍትህ መንገድ ካርታ ........ 36

ለፍርድ ቤት እና ለመንግስት ኤጀንሲዎች የሚገኙበት አድራሻ ........ 37

ለጅማሬ ያህል ........ 49

የዲሲ ክሪሚናል ጀስትስ ሲስተም ካርታ ........ 50

የዲስ የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች ........ 52

የቃላት መፍቻ ........ 59

የክስ መመዝገቢያ ........ 64


በዚህ victimsguide.courtexcellence.org
መስመር (ድረ ገጽ) ላይ በመሄድ መመሪያውን ማግኘት ይቻላሉ።

# ለዲሲ ተጠቂዎች አንገብጋቢ ጉዳዮች

### ለፈጣን እገዛ ወይም ወንጀልን ሪፖርት ለማድረግ ማንን ማግኘት እንደሚገባቹህ።

ተጠቂዎች ፈጣን ድጋፍ ለማግኘት 911 ላይ መደወል አለባቸው። ምንም እንኳን አስቸኳይ ድንገተኛ ጉዳይ ባይኖርም፣ ወንጀሎችን ሪፖርት ለማድረግ እና የፖሊስ ድጋፍ ለማግኘት 911 ላይ መደወል በዲሲ ውስጥ ይፈቀዳል። የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች አስቸኳይ የፖሊስ ያልሆኑ ድጋፎችን ከዲሲ የተጠቂዎች ነፃ መስመር ላይ በመደወል ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

## ለወንጀል ተጠቂዎች አስቸኳይ ቁጥሮች—መጀመሪያ ማን ጋር ይደወል

| | |
|---|---|
| **911** | በጣም አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ያሉ እንደሆነ፣ የድንገተኛ አገልግሎት ለማግኘት፣ ወይም ወንጀልን ሪፖርት ለማድረግ 911 ላይ ይደውሉ። |
| **የዲሲ ተጠቂ ነፃ የስልክ ቁጥር**<br>1-844-4-HELPDC (1-844-443-5732)<br>dcvictim.org | ይሄ የ 24-ሰዓት የፖሊስ ያልሆነ ነፃ መስመር ለሁሉም ለዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች ነፃ እና ሚስጥራዊ መረጃ እና ድጋፍ ያቀርባል። |

## የሕክምና ድጋፍ ያስፈልገኛል

ለድንገተኛ የሕክምና ድጋፍ፣ ተጠቂዎች 911 ላይ መደወል አለባቸው። አስቸኳይ የሕክምና ድጋፍ በአቅራቢያው በሚገኝ ሆስፒታል፣ የድንገተኛ ክፍል፣ ወይም ድንገተኛ እንክብካቤ ማዕከል ውስጥ በመሄድ ማግኘትም ይቻላል። ድንገተኛ ላልሆኑ የሕክምና ድጋፍ ካስፈለጋቸው፣ ተጠቂዎች መደበኛ የሕክምና ሐኪማቸውን ማግኘት ይኖርባቸዋል። ተጠቂዎች መደበኛ ሐኪም የሌላቸው ከሆነ፣ ዲሲ የተጠቂዎች ነፃ መስመር ላይ በመደወል እንዲመደብላቸው ማድረግ ይችላሉ።

## ደህንነት አይሰማኝም

በጣም አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነን ወይም ማስፈራሪያ እየደረሰብን ነው ብለው የሚያስቡ ተጠቂዎች 911 ላይ በመደወል፣ የተመደበላቸውን ተሟጋች፣ የሕግ አስከባሪ፣ እና ወይም ጠበቃቸውን ማሳወቅ ይችላሉ። ያልተፈለገ መቀራረብ ይኖራል ብለው ስጋት ውስጥ የገቡ ሆኖም ግን አስቸኳይ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ያልወደቁ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች እስከ አንድ ዓመት ድረስ አንድን ሰው ከሌላ አቅራቢያ እንዳይደርስ የሚያስችለውን የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲቪክ ፕሮቴክሽን ኦርደር (CPO) ማመልከት ይችላሉ። CPO እንዴት እንደሚገኝ ለበለጠ ለማወቅ ገጽ 30 ላይ ይመልከቱ።

ለዲስ ተጠቂዎች የደህንነት ስሜት መልሰው እንዲያገኙ ሌሎችች ተጨማሪ መረጃዎች አሉ። ለምሳሌ፣ ተጠቂዎች ቁልፋቸውን ለመቀየር ወይም ወደ ሌላ የመኖሪያ ቦታ ሙሉ ለሙሉ እንዲቀይሩ የገንዘብ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይችላል። ስለ የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የካሳ ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ገጽ 25 ን ይመልከቱ። እንደዚሁም ተጠቂዎች ስላለው ድጋፍ ለማወቅ የዲሲ ነፃ የመስመር ስልክ ላይ መደወል ይችላሉ።

## የሕግ ከለላ ያስፈልገኛል

በወንጀል ችሎት ውስጥ፣ የመንግስት አቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ ክስ ይመሰርታል። ሆኖም ግን፣ አቃቤ ሕግ ጥብቅና የሚቆመው ለአንድ የተጠቃ ግልሰብ ሳይሆን ሕዝቡን በመወከል ነው። ሊነሳ ከሚችለው የወንጀለኛ ክስ በተለየ መልኩ ተጠቂዎች የራሳቸውን ፍላጎት እንዲያሟላላቸው እና ከሕግ ጉዳዮች ጋር እገዛ እንዲያደርግላቸው የራሳቸው ጠበቃ ሊፈልጉ ይችላሉ። ስላሉት መረጃዎች ለማወቅ፣ ተጠቂዎች ነፃ ወይም በዝቀተኛ ዋጋ የሕግ ድጋፍ የሚሰጡ ጠበቃዎች ጋር እንዲገናኙ ለወንጀል ተጠቂዎች ድጋፍ ከሚሰጠው ቪክቲም ሌጋል ኔትወርክ ኦፍ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያን (202- 629-1788) ቁጥር ላይ በመደወል አለባቸው።

ጠበቃዎች ለወንጀል ተጠቂዎች የሚከተሉትን ጨምሮ ብዙ ችግሮች ላይ ድጋፍ መስጠት ይችላሉ:

- በሕግ ሂደት ውስጥ ሚስጥራቸውን መጠበቅ;
- በፍርድ ሂደት ውስጥ የመለቀቅ፣ የክስ መልስ ስምምነት፣ የፍርድ ውሳኔ፣ ወይም፣ አመክሮ ጉዳዩች ላይ አስተዋጽኦ ማድረግ;
- የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ማውጣት;
- ከዲስ የተጠቂዎች የካሳ ፕሮጋራም ላይ ለገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ማስገባት;
- ከወንጀል ጋር የተያያዙ የኢምግሬሽን ጉዳዮችን ምላሽ መስጠት; እና
- የሕዝብ ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት።

## ከወንጀል ጋር የተያያዙ ወጪዎች ላይ እገዛ እፈልጋለሁ

አንድ የወንጀል ተጠቂ ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ እንደ የተሰበሩ መስኮቶችን እና በሮችን ማስጠገን፣ ወይም የሚወዱትን ሰው የቀብር ስርዓት ማስፈጸም የመሳሰሉ ነገሮች ፈጣን እርምጃዎች ለመወሰድ ያስፈልገው ይሆናል። ተጠቂዎች ለእነዚህ ዓይነት ወጪዎች እንዲረዳቸው ከዲስ የወንጀል ተጠቂዎች የካሳ ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ናቸው። ስለ የወንጀል ተጠቃሚዎች የካሳ ፕሮግራም በገጽ 25 ላይ የበለጠ ያንብቡ።

## የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂ ነኝ

የዲሲ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎችን ለማገዝ ልዩ መረጃዎች እና አገልግሎቶች አሉ። ለምሳሌ፣ ተጠቂዎች የደህንነት ዕቅድ እንዲያወጡ፣ ጊዜያዊ መኖሪያ እንዲያገኙ፣ ለራሳቸው እና ለልጆቻቸው የማማከር አገልግሎት፣ እና/ወይም የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዞችን እንዲያገኙ የሚደግፉ ተከራካሪዎች አሉ። የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ገጽ 29 ላይ ይሂዱ።

## ወረቀት የሌለኝ ስደተኛ ነኝ

ጥቃት ለደረሰባቸው ወረቀት የሌላቸው ስደተኞች እንደዚሁም እገዛ ይደረጋል። በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ፣ ሜትሮፖሊቲያን ፖሊስ ዲፓርትመንት (MPD) መኮንኖች እንደ የሕገ ወጥ የሰው ዝውውር ጉዳይ ዓይነት አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ  እየመረመሩ ካልሆነ በስተቀር

ስለስደተኞች የኢሚግሬሽን ሁኔታ አይጠይቁም። MPD መኮንኖች ግለሰቡ ተጠቂ ሆነ የጥቃት እማኝ ግለሰብ ቢሆንም፣ የወንጀል ሪፖርት እንዲያደርግ እና ከፖሊሲ እና ከአቃቤ ሕግ ጋር እንዲተባበር ይበረታታል። MPD ያለምንም ወረቀት በዩኤስ ውስጥ ስለሚኖር የወንጀል ተጠቂ ስለሆነ ግለሰብ በጥርጣሬ ብቻ ለፌደራል ኢምግሬሽን ባለስልጣን አሳልፎ አይሰጥም። ከዛ ይልቅ፣ MPD ጥቃት ለደረሰባቸው ወይም የጥቃት ምስክር ለሆኑ ወረቀት ለሌላቸው ስደተኞች ስለሚሰጣቸው ጥበቃ እና ለእነሱ ያሉት ድጋፎች በተመለከተ መረጃ እና ግብአቶችን ማቅረብ አለበት። ሌሎች እንደ ኤፍቢአይ ወይም ሜትሮ ትራንዚት ፖሊስ የመሳሰሉ የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ስለ ከ MPD የተለየ ስለ ወረቀት የሌላቸው ስደተኞች የተለያዩ ፖሊሲዎች ሊኖራቸው ይችላል።

ለ MPD ወንጀል ሪፖርት ከማድረግ በተጨማሪ፣ ወረቀት የሌለው ስደተኛ የሕግ ከለላ ቢጠይቅ አስፈላጊ ነው። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የተከናወነ ወንጀል የወንጀል ተጠቂ የሆነ ወይም ጥቃት ሲፈጸም እማኝ የሆነ ወረቀት የሌለው ስደተኛ ልዩ ጥበቃዎች እንዲደረግለት የሚያስችል ብቁ ሁኔታ ሊያሟላ ይችላል። ተጠቂዎች ከጠበቃ ጋር እንዲገናኙ እና ለቤት ውስጥ ጥቃት ወይም ሌሎች ወንጀሎች ተጠቂዎች እና የወንጀል ጥቃት ሲፈፃም እማኝ ለሚሆኑ ሰዎች ስለሚገኙት ቪዛዎች መረጃ ለማግኘት የቪክቲም ሌጋል ኔትወርክ ኦፍ ዲሲን በዚህ (202-629-1788) ስልክ ማግኘት አለባቸው።

*ይሄ መመሪያ በቀዳሚነት ዋቢ የሚያደርገው የሜትሮፖሊታን ፖሊሲ ዲፓርትመንት (MPD) እንደ መርማሪ አካል ነው፣ ነገር ግን ኤፍቢአይ፣ ዩኤስ ፓርክ ፖሊስ፣ ዘ ሜትሮ ትራንዚት ፖሊሲ፣ እና የ ዩኤስ ፖሊስ ጨምሮ በርካታ የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ይኖራሉ።*

# የዲሲ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ስርዓት ዳሰሳ

ከክስ በፊት ያለው የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ሂደት ........ 7
የክስ ሂደት ........ 11
ከክስ ሂደት በኋላ ........ 17

# ድዲሲ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ስርዓት ካርታ

የዚህን ካርታ የበለጠ በትልቁ ለማየት፣ ገጽ 50 ላይ ይመልከቱ።



ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ልዩ የፌደራል አውራጃ እንጂ ስቴት ስላልሆነ፣ የአካባቢ እና የፌደራል ኤጀንሲዎችን ያካተተ ልዩ የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ስርዓት አለው። በገጽ 6 ላይ ያለው ካርታ የሚያመላክተው ከዚህ በታች በዝርዝር የሚታዩትን አንድ ክስ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዱ በፊት በ ዲ.ሲ የወንጀልኛ ፍትሕ አሰጣጥ ሂደትን ነው። ይሄንን ካርታ በዝርዝር በደንብ ለማየት፣ ገጽ 50 ላይ ይሂዱ።

## ከፍርድ ቤት በፊት ያለው የወንጀለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ሂደት

### *ወንጀልን ሪፖርት ማድረግ*

ወንጀል ሪፖርት ለማድረግ የሚፈልግ ተጠቂ 911 በመደወል ኤምፒዲን ማግኘት ይኖርበታል (ድንገተኛ ጉዳይ ከሌለ ወንጀሎችን ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል)። እንደዚሁም አንዳንድ ወንጀለኞች በድረገጽ ላይ ሪፖርት ሊደረጉ ይችላሉ። [1] ተጠቂዎች የፖሊስ ሪፖርት ማድረጊያ ቁጥሮችን፣ ስሞችን እና ያነገሯቸውን የፖሊስ መኮንኖችን የስልክ ቁጥሮች ለማስረጃነት እንዲረዳቸው መያዝ አለባቸው። ይሄ መረጃ በገጽ 64 ላይ ያለውን የክስ መመዝገቢያ ላይ ሊመዘገብ ይችላል። ወንጀል ሪፖርት በሚደረግበት ጊዜ፣ ኤምፒዲ ተጠቂውን በጠቅላለው የኤምፒዲ የወንጀል ምርመራ ውስጥ ለተጠቂዎች እና ለቤተሰቦቻቸው በዋናነት ከሚያገኟቸው የሲቪል ተጠቂ ስፔሻሊስቶች ከተሞላው የቪክቲምስ ሰርቪስስ ብራንች ጋር ያገናኛል።

### *ምርመራ*

ክሱን ለመመርመር የኤምፒዲ መርማሪ (ስለወንጀሉ በቅድሚያ ክስ የደረሰው የኤምፒዲ ፖሊስ መኮንን ሳይሆን) ይመደባል። አንዳንድ ጊዜ እንደ የወሲብ ጥቃት ቡድን ወይም የሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ባይሴክሸዋል፣ እና ጾታ የቀየሩ ሰዎች ልዩ ቡድን ጉዳዩን ሊመረምር ይችላል። ኤምፒዲ በተቻለ መጠን ምርመራዎችን ለማፋጠን ይሞክራል፣ ሆኖም ግን ጊዜ ይወስዳሉ። ምርመራው በሚካሄድበት ጊዜ፣ ስለ ክስ መዝገባቸው ያለበትን ደረጃ በተመለከተ መረጃ ማግኘት ይችላሉ። አንዳንድ ተጠቂዎች ክሳቸው የተንጓተተ ሊመስላቸው ይችላል። በእውነተኛው ዓለም ውስጥ ያሉ የወንጀል ምርመራዎች በቴሌቪዥን እንደሚታዩት የፖሊስ ድራማ ፊልሞች በፍጥነት ላይጠናቀቁ ይችላሉ።

የተጠቂው ሰው ንብረት ለምርመራ በሚፈልግበት ጊዜ፣ እንደ  የኤምፒዲኤ ማስረጃ ሊያዝ ይችላል። ኤምፒዲ ይሄ አሰራር ምቾት የሚሰጥ እንዳልሆነ ይረዳል እና በተቻለው መጠን ሁሉንም አስፈላጊ

---

[1] አንዳንድ ዓይነት ወንጀሎች ብቻ በድህረ ገጽ ላይ ሪፖርት ሊደረጉ ይችላሉ። እንደ ወንጀል የሚቆጠሩ ወንጀሎችን ሙሉ ዝርዝር ለማየት፣ እና ወንጀልን በድህረ ገጽ ላይ ሪፖርት ለማድረግ፣ እዚህ ይመልከቱ: https://mpdc.dc.gov/service/file-police-report-online.

የሆኑትን ፈተናዎች እና ምርመራዎች ለማጠናቀቅ ይሞከራል። የሚመረምረው መኮንን ለተጠቂው ለምን ንብረቱ እንደተያዘ እና ምን ያህል ጊዜ ኤምፒዲ በማስረጃነት እንደሚይዘው መናገር አለበት።

i

ይሄ መመሪያ በዋነኛነት የሚገልጸው የአዋቂ የወንጀል ፍትሕ አሰጣት ስርዓትን ነው። በዲሲ የወጣቶች ፍትሕ አሰጣጥ ስርዓት ላይ አንዳንድ ቁልፍ ልዩነቶች ይኖራሉ እነዚህም፡

- ምንም ዓይነት አብይ ፍርድ ቤቶች የሉም፡
- የፍርድ ቤት ክሶች የሚታዩት በሚስጥር እና በዝግ ችሎት ነው፡ የተወነጀለው ሰው እና የተጠቂው ሰው የቅርብ ቤተሰቦች ብቻ ሊሳተፉ ይችላሉ፡
- የወጣት ታዳጊ በአመክሮ መውጣት የለም፡ እና
- ስለ ወንጀለኛው ድህረ መለቀቅ ሁኔታ ለተጠቂው የተወሰነ መረጃ ብቻ ይኖረዋል።

ስለ የዲሲ የወጣቶች የፍትሕ አሰጣጥ ስርዓት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ *Guide to the D.C. Juvenile Justice System* ለተባለው ለእንግሊዘኛ እና የስፓኒሽኛ መፅሐፍ courtexcellence.org/ digital-library ይጎብኙ።

## እስራት

ኤምፒዲ ወንጀሉ እንደተፈጸመ ካረጋገጠ በኋላ፣ ተጠርጣሪው መለየት እና ክሱ እንዲቀጥል በእስር መታሰር አለበት። አንዳንድ ጊዜ ተጠርጣሪው ወንጀሉ የተፈጸመበት ቦታ ላይ ሊለይ እና ሊታሰር ይችላል። ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ ክሱ ዓይነት ሳምንታት፣ ወራቶች፣ ወይም ዓመታት ሊወስድ የሚችል ምርመራ ከተደረገ በኋላ እስራት ሊፈጸም ይችላል። አንዳንድ ጊዜ እንደ አጋጣሚ ሆኑ ምንም ተጠርጣሪ ላይገኝ እና ላይታሰር ይችላል።

**ጠቃሚ መረጃ**

ተጠቂው ለፖሊስ ወንጀሉን ሪፖርት ካደረገ፣ እና ቆይቶ አጥቂውን ያየ ከሆነ፣ ለፈጣን የፖሊስ ድጋፍ ተጠቂው 911 ላይ መደወል አለበት። ፖሊሶች በተጠቂው ጥቆማ መሰረት ግልሰቡን የማሰር ስልጣን አላቸው። ተጠቂው የመጀመሪያውን የፖሊስ ሪፖርት ቁጥር ምላሽ ከሰጠው የፖሊስ መኮንን ጋር ማጋራት አለበት። አንገብጋቢ መረጃ ለመቅዳት ከገጽ 64 ጀምሮ የክስ መመዝገቢያ ይጠቀሙ።

## አቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ መመስረት እንዳለበት ይወስናል

አንድ ሰው ከታሰረ በኋላ ከ24 ሰዓት እስከ 28 ሰዓታት ውስጥ፣ ኤምፒዲ የወንጀል ክሶች ወደ ፍርድ ቤት መሄድ እንደሚችሉ ለሚወስነው ለአቃቤ ሕግ ኤጀንሲ የወንጀሉን መረጃ ያቀርባል። በዲሲ ውስጥ፣ ሁለት የአቃቤ ሕግ ቢሮዎች አሉ፡ የአካባቢው ኦፊስ ኦፍ አተርኒ ጀነራል እና የፌደራል ዩኤስ አተርኒ ኦፊስ ፎር ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ (USAO-DC) ናቸው። ስለ እነዚህ ድርጅቶች የበለጠ መረጃ ከታች ይከተሉ። ክሶች ከተከፈቱ፣ በክሱ ጊዜ ሁልጊዜ ድጋፍ የሚሰጥ ለአቃቤ ሕጉ የሚሰራ የተጠቂ ተከራካሪ ይኖራል። ተጠቂው ከአቃቤ ሕግ የሚመጡትን የስልክ ጥሪዎችን እና የጽሁፍ መልዕክቶች ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ነው።

## የወንጀል ክስ መዝገብ ካልተከፈተ

አቃቤ ሕጉ ምንም ዓይነት ክስ ካልመሰረተ፣ የታሰረው ግልሰብ ከእስር መለቀቅ አለበት። ይሄ የተከሰተ ከሆነ፣ ኤምፒዲ ወይም የአቃቤ ሕግ ቢሮ ክሱ ለምን እንደማይመሰረት ለተጠቂው ማስረዳት አለባቸው። ምንም እንኳን ክሱ ባይመሰረትም፣ ተጠቂው አሁንም ቢሆን ከኤምፒዲ የተጠቂዎች አገልግሎቶች ቅርንጫፍ ድጋፍ ማግኘት ይችላል እና ለሪፈራሎች እና መመሪያ የ USAO-DC ተጠቂ እማኝ ድጋፍ ቡድንን ማግኘት ይችላል። እንደዚሁም፣ ተጠቂው ከአጥቂው ከለላ እንዲደረግለት የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ አሁንም መጠየቅ እና የፍትሃብሔር ክስ መመስረት ይችላል። ስለ ሲቪል ጥበቃ ትዕዛዞች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ገጽ 30 ላይ ይሂዱ። ስለ የፍትሃብሔር የህግ ክሶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ገጽ 21 ላይ ይሂዱ።

---

## በዲሲ ውስጥ የሚገኙ የአቃቤ ሕግ ኤጀንሲዎች

### ኦፊስ ኦፍ ዘ አተርኒ ጀነራል ፎር ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ (OAG)

OAG የሚከተሉትን የወንጀል ምድቦች ለፍርድ ያቀርባል:

- የወሲብ ጥቃቶችን ጨምሮ በወጣቶች የፍትሕ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ የሚታዩ የወንጀል ጥቃቶች፥
- ግድ የለሽ የተሽከርካሪ አነዳድን ጨምሮ የትራፊክ አደጋ ጥቃቶችን፥
- አንዳንድ የጦር መሳሪያ  ጥቃቶች፥
- የሕይወት ጥራት ጥቃቶች፣ በበጎ መንፈስ ያልተደረጉትን ጨምሮ፥
- የዲሲ ከተማ ሕግ ጥሰቶች፣ እንደ የመኪና ሰሌዳ ቁጥር ስርቆት፣ እና
- የተመረጡ ማጭበርበሮች፣ የዌልፌር ማጭበርበርን ጨምሮ።

የ OAG የሕዝብ ደህንነት ክፍል የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዞችን መጣስ ለአቃቤ ሕግ ያቀርባል። OAG ለተጠቂዎች እና ለቤተሰቦቻቸው በቅርብ የሚያገለግሉ በተጠቂ እማኝ ስፔሻሊስቶች የተሞሉ የተጠቂ እማኝ ድጋፍ ቡድን አለው።

## ዩኤስ አተርኒ ኦፊስ ፎር ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ (USAO-DC)

USAO-DC የአካባቢውን እና የፌደራል ወንጀሎችን ጨምሮ በዲሲ ውስጥ የሚከናወኑ አብዛኛዎቹን ወንጀሎች ለአቃቤ ሕግ ያቀርባል።

**የ USAO-DC የወንጀለኛ ክፍል የሚከተሉትን ምድብ አይነት የፌደራል ወንጀሎች ለአቃቤ ሕግ ያቀርባል:**

- የብሔራዊ የደህንነት ጥቃቶች፥
- አደገኛ ወንጀሎች እና የአደንዛዥ ዕጽ ዝውውር፥
- ማጭበርበር እና የመንግስት ቢሮ ሙስና፣ እና
- ንብረት መደበቅ እና ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር።

**የ USAO-DC ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክፍል አብዛኛዎቹን በዲሲ ውስጥ ያሉ ወንጀሎችን የሚከተሉትን ጨምሮ ለአቃቤ ሕግ ያቀርባል:**

- ግድያ፣
- የወሲብ ጥቃት፥
- የቤት ውስጥ ጥቃት፥
- ሌሎች አደገኛ ወንጀሎች፥
- ስርቆት፥
- የጦር መሳሪያ ጥቃቶች፣ እና
- የአደንዛዥ ዕጽ ጥሰቶች።

የዩኤስ አተርኒ ኦፊስ የተጠቂዎች እማኝ ድጋፍ ቡድን በፍርድ ቤት ማጀብ፣ የደህንነት ዕቅድ፣ የእማኝ ደህንነት ግምገማ፣ ከከተማ ውጪ ላሉ ተጠቂዎች የጉዞ ማደሪያ ማመቻቸት፣ የስሜት ድጋፍ እና የችግር ምላሽ መስጠት፣ የማሳወቅ አገልግሎት፣ እና ለአማካሪዎች ሪፈራል፣ የቤት፣ የመጓጓዣ፣ የወንጀል የተጠቂዎች የካሳ ቡድን፣ እና የአካል ኣና የአዕምሮ ጤና ፍላጎቶች ጨምሮ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እና እርዳታ ያደርጋል።

# የፍርድ ሂደት

## የመጀመሪያ ችሎት

አንድ ተከሳሽ ለመጀመሪያ ጊዜ በዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ “አሬንመንት” (የቀላል አነስተኛ ወንጀል ክሶች) ወይም “ፕሪዘንትመንት” (ለከባድ ወንጀል ክሶች) ይባላል። በዩኤስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ላይ የሚቀርቡ የመጀመሪያ ችሎቶች የቀላል አነስተኛ ወንጀል ክስ ሆና ለከባድ የወንጀል ክሶች አሬንመንት ይባላሉ። ተጠቂዎች ይሄንን ችሎት ካልፈለጉ በስተቀር ለመሳተፍ አይጠበቅባቸውም። በዚህ ችሎት ላይ፣ የወንጀል ክሶቹ ለተከሳሹ ይነበባል፣ እና ዳኛው ክሱን ለመቀጠል በቂ መረጃ እንደቀረበ ይወስናል። በተጨማሪም ዳኛው ተከሳሹ ይለቀቅ ወይም አይለቀቅ የሚለውን ይወስናል። በቀላል የወንጀል ክስ የታሰሩ ተከሳሾች ዳኛው ወደ ፍርድ ቤት ይመለሳሉ ብሎ ስለሚያስብ አብዛኛውን ጊዜ ይለቀቃሉ። ተከሳሹ ሌላ በእንጥልጥል ያለ የወንጀል ክስ ካለው ወይም ለሌላ የሰራው ወንጀል አመክሮ ላይ ካለ ዳኛው ተከሳሹ እንዲታሰር ሊወስን ይችላል። ለአንዳንድ አደገኛ ከባድ የወንጀል ጥቃቶች፣ እስከ የእስር ችሎት ድረስ ተከሳሹ እንዲታሰር ለአቃቤ ሕጉ ጥያቄ ዳኛው ፈቃድ መስጠት አለበት።

ክሱ ሳይጠናቀቅ ተከሳሹ የሚለቀቅ ከሆነ፣ ዳኛው በኤልክትሮኒክስ ክትትል፣ የቤት ውስጥ እስራት፣ ወይም በማገገሚያ ቤት ውስጥ ጨመሮ የመለቀቅ ሁኔታዎችን ሊያስቀምጥ ይችላል። ክስ እየተከናወነ እያለ በማንኛውም ጊዜ ላይ ተከሳሹ ከተጠቂው ግለሰብ በማንኛውም አይነት ከአቅራቢያው እንዲያደርስ የወንጀለኛ “ርቀትህን ጠብቅ” ትዕዛዝ ዳኛው እንዲያዝ አቃቤ ሕጉ ሊያዝ ይችላል። ዳኛው የርቀትህን ጠብቅ ትዕዛዝ ወሰነ አልወሰነ፣ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂ የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ማግኘት ይችላል። ስለ ሲቪል ጥበቃ ትዕዛዞች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ገጽ 30 ላይ ይሂዱ። በማንኛውም ክፍት ችሎት ላይ ተጠቂው ስለ ተከሳሹ መታሰር የራሱን አስተያየት የመስጠት መብት አለው። ለወንጀል ተጠቂ መብቶች ሙሉ ዝርዝር፣ ገጽ 52 እስከ 56 ላይ ይመልከቱ።

i

አንድ የክስ መዝገብ ወደ ችሎት ከተወሰደ፣ የክስ መዝገቡን በተመለከተ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ በተከሳሹ ጠበቃ ተከሳሹን የማግኘት ጥረት ሊኖር ይችላል። ተጠቂው የተከሳሹን ጠበቃ ለማናገር ሆነ ላለማናገር መወሰን ይችላል። ተጠቂው ከተከሳሹ ጠበቃ ጋር በሚኖረው ንግግር ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ያሉት ከሆነ፣ ተጠቂው ተጠቂው የራሱን ተከራካሪ ወይም አቃቤ ሕጉን ማግኘት አለበት።

## ቅድመ ችሎት የእስራት ክስ መታየት

ዳኛው ተከሳሹ አስቀድሞ በእስር እንዲቆይ የወሰነ ከሆነ፣ ሌላ ችሎት ከ 3 እስከ 5 ቀናት ውስጥ ይከናወናል። በዚህ ችሎት ላይ፣ ሌላ ዳኛ ተከሳሹ በእስር ይቆይ ወይም ተከሳሹ ከቅድመ ሁኔታዎች ጋር ይፈታ የሚለውን ይወስናል። እነዚህ ሁኔታዎች የተጠቂውን እና የማህበረሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ የተነደፉ ናቸው፣ እና ተከሳሹ ወደ ፍርድ ቤት እንደሚመለስ ለማረጋገጥ ነው። ከዚህ ሁለተኛ ችሎት በኋላ ከዚህ ቀደም በእስር የቆየ ተካሳሽ የመለቀቀ ሁኔታ ያልተለመደ ነገር ነው።

## የመጀመሪያ ችሎት – አሳማኝ ምክንያት ይኖራል?

በከባድ የወንጀል ክሶች ወቅት፣ ከመጀመሪያው የቅድመ ችሎት በኋላ የመጀመሪያው ችሎት ተከሳሹ መብቱን ካላነሳ በስተቀር ከ20 ቀናት በላይ መውሰድ የለበትም። በዚህ ችሎት ወቅት፣ ተከሳሹ ወንጀሉን እንደፈጸመ በቂ ማስረጃ ወይም "የሚያስገድድ ምክንያት" እንዳለው እና እንደሌለው ዳኛው ብይን ይወስናል። አቃቤ ሕጉ በተለምዶ በክስ መዝገብ ውስጥ ያሉትን ነጥቦች እንዲመሰክር ለፖሊሲ መኮንኑ ይደውላል።

የመጀመሪያው ችሎት ላይ፣ ዳኛው የሚያስገድድ ምክንያት ካላገኘ፣ ክሱ ይቋረጣል። ክሱ ከተቋረጠ፣ አቃቤ ሕጉ ተጨማሪ መረጃ ሊያሰባስብ እና ተከሳሹን በድጋሚ ሊከስ ይችላል። ዳኛው አስገዳጅ ምክንያት አለ ብሎ የሚያምን ከሆነ፣ ክሱ ወደ በላይ ፈራዶ ይላካል።

## የበላይ ፈራዶ ኢንዳይትመንት መስጠት እንዳለበት ይወስናል

በከፍተኛ የወንጀል ክሶች፣ ምንም እንኳን ዳኛው በመጀመሪያ ችሎት ላይ አስገዳጅ ምክንያት ቢያገኝም፣ ህጉ በበላይ ፈራዶ ውስጥ ሁለተኛ አስገዳጅ ምክንያት እንዲኖር ይጠይቃል። ከበቂ ምክንያት በላይ የወንጀል ተከሳሹ መሆኑን ከሚወስነው "ጥቃቅን" ወይም አነስተኛ ችሎት፣ ፍርድ ቤት በተለየ መልኩ የበላይ ፈራዶ ልዩ ነው። የበላይ ፈራዶ ችሎት ዝግ ናቸው፣ ይሄም ማለት ተጠቂውን ጨምሮ ማንኛውም የማህበረሰቡ አካል ለፍርድ ቤት ቃል እንዲሰጥ ካልተፈለገ በስተቀር መግባት አይቻልም። የተወነጀለው ሆና ጠበቃውም ፍርድ ቤት ውስጥ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም። የበላይ ፈራዶ በአቃቤ ሕጉ በተወነጀለው ግለሰብ ላይ የቀረበውን ማስረጃ ያዳምጥና ወንጀለኛው ወንጀሉን ስለመፈጸሙ የሚያሳምን አስገዳጅ ምክንያት ቀርቧል ወይስ አልቀረበም የሚለውን ይወስናል። ማስረጃው በቂ ከሆነ፣ በወንጀለኛው የተፈጸመው ወንጀል (ሎች) የሚያብራራ የጽሁፍ ማዘዣ የክስ ረቂቅ የሆነውን "indictment" (የሚነበበውም "ኢን-ዳይት-መንት") ትዕዛዝ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ያወጣል። ማስረጃው በቂ ሆኖ ካልተገኘ፣ በወንጀለኛው ላይ የተነሱት ክሶች ይነሳሉ። ኢንዳይትመንት ለማግኘት፣ ተጠቂው ከበላይ ፈራዶ ፊት ቆሞ ቃሉን መስጠት ይጠበቅበታል። በዚህ ጊዜ፣ ተጠቂው ግለሰብ

ቀን፣ ሰዓት፣ እና በየትኛው የበላይ ፈራዶ ፊት መገኘት እንዳለበት የሚናገር መጥሪያ (የፍርድ ቤት ቅረብ ማዛዣ) ይደርሰዋል።

## አሬንመንት

የበላይ ፈራዶ ወንጀለኛውን (አሁን ተከሳሽ) ኢንዳይት ካደረገው፣ የከፍተኛ ወንጀል አሬንመንት መርሀ ግብር ይያዛል። በዚህ ችሎት ላይ፣ ተከሳሹ ስለቀረበበት ክስ ማብራሪያ ይሰጠዋል፣ ስላለው ሕገ መንግስታዊ መብቶች ይነገረዋል፣ እና የእምነት የክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ይጠይቃል። ተከሳሹ "ያለምንም ተቃውሞ" ክሱን መቀበል፣ ማለትም ተከሳሹ ለክሶቹ ሃላፊነት እንደሌለው አምኖ የሚደርስበትን ቅጣት ለመቀበል መስማማት ነው።

አንዳንድ ጊዜ በተከሳሹ እና በአቃቤ ሕጉ ስምምነት መሰረት፣ በዚህ ችሎት ላይ ተከሳሹ ክሱን ሊያምን ይችላል። ተከሳሹ ወንጀሉን የሚያምን ከሆነ፣ አነስተኛ ክሶችን ለማግኘት፣ ወይም አነስተኛ ቅጣት እንዲበየንበት አቃቤ ሕጉ ከተከሳሹ ላይ አንድ ወይም ከዛ በተጨማሪ ያሉ ክሶችን ሊያነሳለት ይችላል። በአንዳንድ አነስተኛ የወንጀል ክሶች፣ እንደ የምክር አገልግሎት እና/ወይም የማህበረሰብ አገልግሎት የመሳሰሉ፣ አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማከናወን ተስማምቶ፣ ለጥቃቱ መፈጸም ድርጊቱን አምኖ፣ ፍርድ ቤት ሄዶ የመከራከር መብቱን ካነሳ በኋላ፣ አቃቤ ሕጉ የተለየ የቅጣት አካሄድ ለፍርድ ቤቱ ሊያቀርብ ይችላል።፣ ተከሳሹ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ካጠናቀቀ፣ ፍርድ ቤቱ የወንጀለኛነት የእምነት ቃሉን እንዲያነሳ ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ ይፈቅዳል እና ሁሉንም ክሶች መንግስት ያነሳል። ተከሳሹ ቅድመ ሁኔታዎቹን የማያነሳ ከሆነ፣ የየሰጠው የወንጀል መፈጸም የእምነት ቃል በቋሚነት የተከሳሹ መዝገብ ላይ እንዲሰፍር ተደርጎ፣ ተከሳሹ በፍርድ ቤቱ የእስር፣ የማህበረሰብ ክትትል፣ ወይም የገንዘብ ቅጣት እንዲፈጽም ይፈረድበታል።

ዳኛው የተከሳሹን የእምነት ቃል ከመቀበሉ በፊት፣ ዳኛው ተከሳሹ ስላለው መብት እርግጠኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተከሳሹ የእምነት ቃሉን የሚሰጠው ከፍራቻ ወይም ካለበት ጭንቀት የተነሳ አለመሆኑን እንዲያረጋግጥ ይጠይቀዋል። ዳኛው ያለምንም ተቃውሞ የእምነት ቃል ከተቀበለ፣ ተጨማሪ የፍርድ ሂደቶች አይኖሩም፣ እና ተከሳሹ በሌላ ችሎት ላይ ብይን ይሰጠዋል። በአነስተኛ የወንጀል ክስ፣ ፍርድ የሚሰጠው በጥቂት ቀናት ወይም ሳምንታት ውስጥ ነው። ከባድ የወንጀል ድርጊት ከሆነ፣ ፍርዱ በተለምዶ የሚሰጠው ቢያንስ ከስድስት ሳምንታት በኋላ ነው። ስለ ፍርድ አሰጣጥ የበለጠ ለማወቅ ገጽ 15 ላይ ይመልከቱ።

## የአቋም ችሎት

ተከሳሹ የክህደት ቃሉን የሰጠ ከሆነ፣ በክስ መዝገቡ ላይ ስላለው ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እና ጠበቃዎቹ ለፍርዱ ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ "የአቋም ችሎት" የተባሉ አንድ ወይም ከዛ በላይ ቅድመ ችሎቶችን ዳኛው ያከናወናል። የፍርድ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት አንዳንድ ጉዳዮችን ለማጥራት

የአቤቱታ ችሎት ሊደረግ ይችላል። ለምሳሌ፣ የተከሳሹ ጠበቃ ፖሊስ ሕግ መንግስቱን በሚፃረር መልኩ አንዳንድ ማስረጃዎችን አቅርቧል እና ከችሎቱ መነሳት አለበት በሚል የቅድመ ችሎት አቤቱታ ሊያነሳ ይችላል።

ጠቃ

የምስክርነት ቃል አሰጣጥ ጠቃሚ መረጃ

- ሁልጊዜ እውነቱን ይናገሩ።
- እያንዳንዱን ጥያቄ በጥንቃቄ ያዳምጡ እና ከመመለስዎ በፊት በትክክል እንደተረዱት ያረጋግጡ። ጥያቄው እንዲደገም መጠየቅ ምንም ችግር የለውም።
- ዳኛው ካልጠየቅዎ በስተቀር መልሶችን በግምት አይመልሱ ወይም አስተያየትዎን አይስጡ። ለተጠየቁት ጥያቄ መልሱን የማያውቁ ከሆነ፣ አላውቅም ብለው ይመልሱ።
- መልሶችዎን አይሸምድዱ።
- በፍርድ ቤት ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው እንዲያደምጥዎ በረጋ እና በከፍታ ድምጽ ይናገሩ።
- ለመረጋገት የተቻሎትን ያድርጉ ምንም እንኳን ጠበቃው ቢያበሳጭዎት ወይም ስሜትዎን ለመንካት ቢሞክር፣ ላለመበሳጨት ይሞክሩ።
- ዳኛውን ያዳምጡ። ከጠበቃዎቹ አንዱ ተቃውሞ ቢያሰማ፣ ዳኛው እንዲቀጥሉ እስከሚነግርዎ ድረስ ቃሎትን መስጠት ያቁሙ።
- ግራ ከተጋቡ ወይም ጥያቄ ያሎት ከሆነ፣ ዳኛው እንዲያግዞት እርዳታ ይጠይቁ።

## ችሎት

ተከሳሹ የክህደት ቃሉን የሰጠ ከሆነ፣ ችሎት ይጀመራል። የችሎቱን ቀን፣ ሰዓት፣ እና ቦታ በአቃቤ ሕግ ቢሮ በኩል ለተጠቂዎች ይገለፃል። ተጠቂዎች እያንዳንዱን ችሎት ላይ መገኘት አይጠበቅባቸውም፣ ነገር ግን ቃል ለመስጠት የሚፈለጉ ከሆነ መገኘት አለባቸው።

በከባድ ወንጀል የተከሰሱ ተከሳሾች እራሳቸውን ለመከላከል ሌላ ቀጠሮ ሊጠይቁ ይችላሉ፣ እና ለአብዛኛዎቹ የአነስተኛ ወንጀል ክሶች የመጨረሻው ውሳኔ ወይም "ብያኔ" በዳኛው ይደረጋል። በችሎቱ ጊዜ፣ አቃቤ ሕጉ ማስረጃዎችን ያቀርባል እና ምስክሮቹ የሚጠየቁበት ቦታ ላይ ቀጥተኛ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። ከዛም የተከሳሹ ጠበቃ የማመሳከር ጥያቄ የሚባለውን የአቃቤ ሕጉን ምስክሮች ይጠይቃል። የአቃቤ ሕጉ የክስ መዝገብ ቀረበ በኋላ፣ የተከሳሹ ጠበቃ ማስረጃ ሊያቀርብ ወይም ምስክር ሊጠራ ይችላል፣ ሆኖም ግን አያስፈልግም፣ ምክንያቱም አቃቤ ህጉ ክሱን ለማጠናቀር ሲል ሃላፊነቱን ስለሚወጣ ነው። ተከሳሹ

ዝም የማለት እና ቃሉን ያለመስጠት ሕገ መንግስታዊ መብት አለው። ተከሳሹ ቃሉን ለመስጠት የመረጠ እንደሆነ፣ አቃቤ ሕጉ ተከሳሹን የማመሳከሪያ ጥያቄ ለመጠየቅ ይፈቀድለታል። ተከሳሹ

ማስረጃ የማያመጣ ከሆነ፣ አቃቤ ሕጉ ሁሉንም የተከሳሽ ምስክሮችን በማመሳከሪያ ጥያቄ የመጠየቅ እና "የሚያፋልስ ማስረጃ" በማቅረብ ምላሽ የመስጠት መብት አለው።

## ብያኔ – ወንጀለኛ ወይም ከወንጀል ነፃ?

በችሎቱ መጨረሻ ላይ፣ ዳኛው ወይም ፈራዶዎች ያለምንም ጥርጥር ተከሳሹ ወንጀለኛ እንደሆነ በአቃቤ ሕጉ ተረጋግጧል ብለው ካመኑ ብያኔአቸውን ይሰጣሉ። ፈራዶዎቹ ውሳኔ በሚሰጡበት ሰዓት፣ "ዴሊበሬሽን" ይባላል። ሁሉም ፈራዶዎች ብያኔው ላይ መስማማት አለባቸው። ፈራዶዎቹ የማይስማሙ ከሆነ፣ ወይም አንዱ ፈራዶ እንኳን የማይስማማ ከሆነ፣ ምንም ብያኔ የለም። ይሄ "ሃንግጁሪ" ወይም "ሚስትሪያል" ይባላል። የሃንግጁሪ ወይም የተንጠለጠለ ክስ የሚኖር ከሆነ፣ አቃቤ ሕጉ በድጋሚ ተከሳሹን ለፍርድ ማቅረብ፣ አዲስ የእምነት የክህደት ቃል እንዲሰጥ መጠየቅ፣ ወይም ክሱን ማቋረጥ ይችላል። ተከሳሹ ወንጀለኛ መሆኑ ከታወቀ፣ ፍርድ የሚሰጥበትን ቀን ዳኛው ይወስናል እና እስከ ችሎቱ ድረስ በእስር ቤት ውስጥ ተከሳሹ (አሁን ወንጀለኛ ተብል የሚጠራው) እንደሚቆይ ወይም እንደማይቆይ ይወስናል። ማንኛውም ጥያቄ ለመመለስ ክሱ ከተጠናቀቀ በኋላ አቃቤ ሕጉ ከተጠቂው ጋር መገናኘቱን ይቀጥላል፣ እና ከአቃቤ ሕግ ቢሮ ያለው የተጠቂው ተሟጋች ተጠቂውን ለማገዝ የሚገኝ ይሆናል።

ተከሳሹ ከወንጀል ነፃ ነው ከተባለ፣ ተከሳሹ "ይፈታና" ነፃ ይሆናል። ምንም እንኳን ክሱ ቢቋረጥም፣ ተጠቂዎች የሲቪክ ጥበቃ ትዕዛዝ የመጠየቅ መብት አላቸው፣ ወይም ክሱን በፍትሐብሄር እንዲታይላቸው ተከሳሹን መክሰስ ይችላሉ። ስለ ዲሲ የፍትሐብሄር የፍትሕ አሰጣጥ ስርዓት የበለጠ መረጃ ከገጽ 21 ጀምሮ ማግኘት ይቻላል።

## የፍርድ ብያኔ ችሎት

ወንጀለኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም ወንጀለኛነቱን ሲያምን፣ ዳኛው የፍርድ ብያኔ ቀን ይቆርጣል። ተጠቂዎች፣ ፍርድ የሚሰጥበት ቀን ላይ ለመገኘት መምረጥ ወይም አለመምረጥ ይችላሉ። የፍርድ ብያኔ ከመሰጠቱ በፊት፣ ዘ ኮርት ሰርቪስ ኤንድ ኦፈንደር ሱፐርቪዥን ኤጀንሲ (CSOSA) ለዳኛው ቅድመ ብያኔ ሪፖርት ያቀርባል። ይሄ ሪፖርት የሚያካትተው ስለተከሳሹ መረጃ እና የቅድመ ብያኔ ሪፖርት ከመጠናቀቁ በፊት ተጠቂው የፃፈው የተጠቂ ጉዳት ሀተታ ነው። እንደዚሁም የተጠቂ ጉዳት ሀተታዎች በአቃቤ ሕጉ በኩል ወይም ደግሞ በቀጥታ ለዳኛው ሊቀርቡ ይችላሉ። ተጠቂ በተጨማሪም

**የተወነጀለ**
ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የሚጠረጠር ግለሰብ ሆኖም ግን በፍርድ ቤት ያልተረጋገጠበት ግለሰብ።

**ተከሳሽ**
ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ክስ የተመሰረተበት ግለሰብ።

**ወንጀለኛ**
ወንጀል እንደፈጸመ የተረጋገጠበት ግለሰብ።

ከፅሁፍ ሀተታው በተጓዳኝ ወይም በእርሱ ፈንታ የተጠቂ ጉዳት ሀተታን በፍርድ ብያኔ የሚሰጥበት ቀን ላይ በቃል ማቅረብ ይችላል።

የፍርድ ብያኔ በሚሰጥበት ጊዜ፣ አቃቤ ሕጉ እና የተከሳሹ ጠበቃ እንደ ለምን ወንጀሉን ለመፈጸም እንደተገደደ የሚያመላክቱ የወንጀለኛውን ግለሰብ የወንጀል ታሪክ አዝማሚያ የሚጠቁሙ መረጃዎችን ያቀርባሉ። የሚፈልጉ ከሆነ ተጠቂዎች የፍርድ ብያኔ ቀን ላይ ያላቸውን ሐሳብ የማስተላለፍ መብት አላቸው። ችሎቱ ከተጠናቀቀ ብኋላ፣ ዳኛው ተከሳሹ ላይ የፍርድ ብያኔ ይሰጣል።

---

## የተጠቂ ጉዳት ሀተታ

በወንጀል ክስ ሂደቶች ላይ፣ ተጠቂው የፍርድ ብያኔ ከመሰጠቱ በፊት፣ ማንኛውንም በተጠቂው ላይ የተፈጸሙ ወይም የተከሰቱ የስሜት፣ የአዕምሮ፣ የገንዘብ፣ ወይም የአካል ጉዳት የሚገልጽ የተጠቂ ጉዳት ሀተታ የማቅረብ መብት አለው። ተገቢውን ፍርድ ብያኔ እንደተሰጠ ለማረጋገጥ ዳኛው የተጠቂውን የጉዳት ሀተታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ውሳኔ ይሰጣል። ከፅሁፍ ሀተታው በተጓዳኝ ወይም በእርሱ ፈንታ የተጠቂ ጉዳት ሀተታን በፍርድ ብያኔ የሚሰጥበት ቀን ላይ በቃል ማቅረብ ይችላል። የተጠቂው ተሚጋቾች እነዚህን ሃተታ ጽሁፎች እንዲያዘጋጅ ለተጠቂው ሊያግዙት ይችላሉ። የተጠቂው የጉዳት ሀተታ የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡

- እንዴት ወንጀሉ ተጠቂውን እና ቤተሰቡን እንደጎዳ፥
- በተጠቂው እና በተጠቂው ቤተሰብ መሃል ያለውን ስሜታዊ ጉዳት፥
- በተጠቂው እና በቤተሰቡ ላይ ያመጣውን የገንዘብ ጉዳት፥
- ወንጀለኛው እንዴት መቀጣት እንዳለበት የሚገልጽ የተጠቂው አስተያየት፥ እና
- ተጠቂው ለፍርድ ቤቱ ለመናገር የሚፈልገው ማንናውም ሌላ ነገር።

---

የፍርድ ብያኔ በሚሰጥበት ሰዓት፣ ዳኛዎች መደበኛ የፍርድ ብያኔ አሰጣጥ መመሪያዎችን ይከተላሉ ሆኖም ግን አንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎችን ከግምት ያስገባሉ። ዳኛው ቀላል ፍርድ ለመስጠት ጥሩ ምክንያት ሊያገኝ ወይም ወንጀሉ በጣም የከፋ ሆነ ጠንከር ያለ ብያኔ ሊሰጥ ይችላል። ለአንዳንድ ወንጀሎች፣ በህግ ከተቀመጠው የእስር ጊዜ ያላነሰ ውሳኔ ዳኛው እንዲሰጥ የሚያስገድዱ አስገዳጅ ዝቅተኛ የእስር ጊዜያቶች አሉ።

## ከወንጀል ችሎቱ በኋላ

### የዲስ ወንጀለኞች የት እንደሚታሰሩ

ዳኛው ወንጀለኛውን በእስር እንዲቀጣ ብያኔ ካስተላለፈበት፣ እንደ የእስር ጊዜው ርዝማኔ፣ ተከሳሹ እንደ አዋቂ ወይም ወጣት ታዳጊ እንደተከሰሰ ወይም ወንጀሉ የአካባቢ ወይም የፌደራል ጥቃት እንደሆነ፣ እና ሌሎችም ምክንያቶች መሰረት ተከሳሹ ሊታሰርባቸው የሚችሉ ብዙ ማረሚያ ቤቶች አሉ።

---

### ሴንተራል ዲቴንሽን ፋሲሊቲ

የሴንተራል ዲቴንሽን ፋሲሊቲ እንደዚሁም የዲስ ማረሚያ ቤት በመባል ይታወቃል ፣ ለአዋቂ ቅድመ ችሎት ተከሳሾች እና ከአንድ ዓመት በታች የተፈረደባቸው አዋቂዎች የሚታሰሩበት ዋና እስር ቤት ነው።

### ኮሬክሽናል ትሪትመንት ፋሲሊቲ

ሴቶችን፣ እንደ አዋቂ የተከሰሱ ወይም የተፈረደባቸው ታዳጊ ወጣቶችን፣ እና አስጊ የጤና እክል ያለባቸው ሰዎች የመሳሰሉ የተለዩ የማህበረሰቡ አባላትን የያዘ ከዲስ ማረሚያ ቤት ቀጥሎ የሚገኝ የተለየ ማረሚያ ቤት ነው።

### ፌደራል ቢሮ ኦፍ ፕሪዝንስ

አንድ እና ተጨማሪ ዓመት የጽኑ ኣስራት የተፈረደባቸው የዲሲ አካባቢ ሰዎች የሚታሰሩበት ቦታ በመላው ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በፌደራል ቢ ሮ ኦፍ ፕሪዝንስ ፋሲሊቲስ ውስጥ ነው። በዲሲ ውስጥ የፌደራል ወንጀሎችን ፈጽመው የተገኙ ሰዎች እና በማንኛውም የእስር ጊዜ የተፈረደባቸው ሰዎች የሚተሳሩት በእነዚህ በእነዚህ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ነው።

### የዲሲ ዩዝ ሰርቪስስ ሴንተር

ይሄ ማረሚያ ቤት በታዳጊ ወጣቶች የፍትህ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ የፍርድ ብይን የሚጠባበቁ ወንድ እና ሴት ታዳጊ ወጣት ወንጀለኞችን ይያዛል።

### ኒው ቢግኒንግስ ዩዝ ዴቨሎፕመንት ሴንተር

ይሄ ማረሚያ ቤት እስከተፈረደባቸው የእስር ጊዜ ድረስ የተፈረደባቸውን የወንድ እና ሴት ወንጀለኛ ታዳጊ ወጣቶችን ይይዛል።

---

መረጃት እና የማረሚያ ዝውውር ጨምሮ ለተጠቂዎች የታሳሪዎችን አቋም ለውጥ የሚያሳውቀውን የራስሰር የተጠቂ ማሳወቂያ ስርዓት ቪክቲም ኢንፎርሜሽን ኤንድ ኖትፊኬሽን ኤቨሪዲ (VINE) ስርዓትን በመጠቀም የታሰሩ ሰዎች ያሉበትን ቦታ ሰዎች ማወቅ ይችላል። የታሰረ ወይም በቅርቡ የተፈታን ወንጀለኛ ለማግኘት፣ ወይም የራስሰር VINE ማሳወቂያዎችን ለማስመዝገብ፣ በ 1-877-329-7894 ላይ ይደውሉ ወይም ይሄንን ይጎብኙ vinelink.com.

## ዘ ቪክቲም ኢንፎርሚሽን ኤንድ ኖትፊኬሽን ኤቭሪዴይ (VINE) ስርዓት

ቫይን (VINE) የዲሲ ማረሚያ ቤቶች መምሪያ ፋይሎችን መፈታት፣ የማረሚያ ቤት ዝውውር፣ የፍርድ ቤት ችሎት፣ ወይም በድጋሚ መታሰርን ጨምሮ የታሰሪዎች የእስር አቋም ለውጥ
በተከታታይ ይከታተላል። የእስር አቋም ለውጥ አንዴ ከተደረገ፣ የቫይን ስርዓት ተጠቂዎች ያስመዘገቡትን ስልክ ቁጥሮች ወይም ኢሜይል አድራሻዎች ላይ በራስሰር የስልክ ጥሪ በማድረግ ወይም በኢሜይል ያሳውቃል።
የተመዘገቡ ተጠቂዎች ስለእስረኛ ወቅታዊ የአቋም መረጃ ለማግኘት በ **1-877-329-7894** ላይ መደወል ይችላሉ። የቫይን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት ለመመዝገብ፣ **1-877-329-7894** ላይ ይደውሉ ወይም **vinelink.com**.

## የማህበረሰብ ክትትል

ዳኛው ተከሳሹን ከፍርድ ቤት ይልቅ ወደ የማህበረሰብ ክትትል (በአብዛኛውን አመክሮ ጊዜ ተብሎ የሚታወቀውን) ሁኔታ ውስጥ ይልከዋል፣ ይሄም ማለት ተከሳሹ ከእስር ይፈታል ነገር ግን አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያሟላ ይጠበቃል። ዳኛው እንደዚሁም አንድን ተከሳሽ ለተወሰነ ጊዜ ያህል እንዲታሰር እና ከዛም ወደ የማህበረሰብ ክትትል ውስጥ (በተልምዶ አመክሮ ተብሎ የሚታወቀው) ፕሮግራም ውስጥ ሊያስገባው ይችላል። የማህበረሰብ ክትትል ቅድመ ሁኔታዎች የሚያካትቱት፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም፣ ለኮርት ሰርቪስስ ኤንድ ሱፐርቪዥን ኤጀንሲ (CSOSA) ሁልጊዜ በየሳምንቱ ሪፖርት ማቅረብ፣ የኤልክትሮኒክስ መቆጣጠሪያ፣ ሰዓት ዕላፊ፣ የአደንዛዥ ዕጽ/የመጠጥ ፍተሻ እና ሕክምና፣ እና ከተጠቂው ጋር ምንም አይነት ቅርብርብ እንዳያደርግ የመሳሰሉት ናቸው።

i

ዳኛው የፈረደው **የርቀት የመጠበቅ ትዕዛዝ** ከፍርድ ብይን በኋላ ይቋረጣል፣ ነገር ግን ዳኛው የተከሳሹን የሙከራ ጊዜ ወይም አመክሮ ላይ ርቀት የመጠበቅን ትዕዛዝ እንደ ቅድመ ዕይታ ሊያስቀምጥ ይችላል። ይሄ ከሆነ የተፈረደው፣ ከእስር መለቀቅ በኋላ ቅርርብ መፍጠር ወደ እስር ቤት መልሶ የሚያስገባ የህግ ጥሰት ነው።

በዲሲ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ችሎት ማህበራዊ አገልግሎቶች ዲቪዚዮን በኩል ክትትል የሚደረግባቸው ከታዳጊ ወጣት ወንጀለኞች በስተቀር፣ በማህበረሰብ ክትትል ላይ ያሉ አብዛኛዎቹ የዲሲ ወንጀለኞች ክትትል የሚደረግባቸው በ CSOSA ነው። የ CSOSA የማህበረሰብ ክትትል መኮንን ከፍርድ ቤት ከተበየኑት መስፈርቶችን እያከበረ መሆኑን ለማረጋገጥ ወንጀለኛውን ይከታተላል። CSOSA ለተጠቂዎች እገዛ የሚሰጥ የተጠቂ አገልግሎቶች ፕሮግራም አለው፣

ከሁሉም በላይ ደህንነታቸውን መጠበቁን እና ሁሉንም ግብአቶች ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ነው። በ CSOSA አንድ ወንጀለኛ ክትትል እየተደረገበት ከሆነ፣ የተጠቂውን ፍላጎት፣ ከደህንነት ዕቅድ ጋር ማገዝ፣ እና ለአስፈላጊ አገልግሎቶች ሪፈራል መስጠት ላይ ለተጠቂው ድጋፍ የሚሰጠው CSOSAን ተጠቂው ማግኘት አለበት።

## አንድ ወንጀለኛ የማህበረሰብ ክትትል ውሎችን የጣሰ ከሆነ

አንድ ወንጀለኛ የማህበረሰብ ክትትልን ውሎች ከጣሰ፣ የክትትል መኮንኑ ዳኛውን ሊያሳውቅ ይችላል እና "የተጨማሪ ማስረጃ ችሎት" ሊጠይቅ ይችላል። በተጨማሪ ማስረጃ ችሎት ላይ፣ ተከሳሹ የተከሳሹ የማህበረሰብ ክትትል ለምን መነሳት እንዳለበት ለዳኛው የመግለጽ ዕዳ አለበት። ዳኛው የተከሳሹን የማህበረሰብ ክትትል ለመሰረዝ የወሰነ እንደሆነ፣ ዳኛው ያኔ በድጋሚ ተከሳሹ ላይ አዲስ ብያኔ ይሰጣል እና በጣም ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ ወይም የዳግመኛ እስራት ጊዜ ፍርድ ሊሰጥ ይችላል። ተጠቂው በዚህ ችሎት ላይ የመገኘት መብት አለው እና ቃሉን እንዲሰጥ ሊጠየቅ ይችላል።

## የወንጀል ውሳኔን ይግባኝ ማለት

ተከሳሾች አንዴ ወንጀለኛ ተብለው ከተፈረደባቸው በኋላ ስለፍርድ ይግባኝ መጠየቃቸው የተለመደ ነው። እነዚህ ይግባኞች በአብዛኛው ስለ ማስረጃ እና የፈራዶ መመሪያዎችን ጨምሮ እንደ የፍርድ ቤት አካሄድ እና የዳኛው ውሳኔ ላይ ያተኮሩ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ነው። በዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ የሚደረጉ ይግባኝ ጥያቄዎች የሚከናወኑት በዲሲ ኮርት ኦፍ አፐሊስ ውስጥ ነው። በዩኤስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ውስጥ የሚነሱ የውሳኔ ይግባኞች የሚሰሙት በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የዩኤስ ኮርት ኦፍ አፒልስ ላይ ነው።

ይግባኝ ጥያቄ በሚታይበት ወቅት፣ ሰበር ችሎቱ የሚገመግመው የተፃፈውን የክስ መዝገብ ብቻ ነው፣ እና በይግባኝ ጊዜ ምንም ዓይነት ማስረጃ ወይም ምስክርነት አይሰጥም። ለአቃቤ ሕግ እና ለተከሳሹ የቆሙ ጠበቆች ስለ ይግባኙ በተመለከተ ያላቸውን መከራከሪያ ነጥብ የሚያጎላ አጭር ማብራሪያ ጽሁፍ ፋይል ያደርጋሉ። ፍርድ ቤቱ የአቃቤ ሕግ ጠበቃ እና የተከሳሹ ጠበቃ በዳኞች ፓናል ፊትለፊት መከራከሪያ ነጥቦቻቸውን ማንሳት እና መልስ የሚመልሱበት የቃል ክርክር የሚደረግበት የችሎት መርሀ ግብር ሊያዘጋጅ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ይሄንን ክፍት ችሎት ተጠቂዎች መከታተል ይችላሉ። ከዚህ ችሎት በኋላ፣ ይግባኙ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ፍርድ ቤቱ ብዙ ወራት ሊፈጅበት ይችላል። ፍርድ ቤቱ ይግባኙ ላይ በሦስት ዓይነት መንገድ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል።

## የወንጀል ይግባኞች ሊኖራቸው የሚችለው ውጤት

### ጸንቷል

የይግባኝ ብይን ሰጪ ፍርድ ቤቱ ውሳኔው እንዲጸና ይወስናል።

### ተቀልብሷል

የይግባኝ ብይን ሰጪ ፍርድ ቤት ውሳኔው ኣንዲቀለበስ ያዛል።

### ተቀልብሶ እንዲሻሻል

የይግባኝ ሰጪ ፍርድ ቤት ውሳኔው ስህተት አለበት ብሎ በመወሰን ለበታች ፍርድ ቤት በአዲስ ችሎት እንዲታይ ሊመራ ወይም ተጨማሪ ሌሎች እርምጃዎች ኣንዲወሰዱ ሊያዝ ይችላል።

# የዲሲ የፍትሃብሔር የፍትህ አሰጣጥ ስርዓት

ከወንጀል የፍትህ አሰጣጥ ስርዓቱ በተጨማሪ፣ ተጠቂዎች በዲሲ የፍትሃብሔር የፍትህ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ መፍትሔ ሊያገኙ ይችላሉ። የወንጀል እና የፍርሃብሔር ፍትህ አሰጣጥ ስርዓቶች የተለያዩ የፍትህ አሰጣጥ ሂደቶች ናቸው። የፍትሃብሔር ክስ መመስረት የወንጀል ክስ መክሰስ ላይ ችግር አይፈጥርም—የፍትሃብሔር ክሶች ከወንጀል ችሎት በፊት፣ ወቅት ወይም በኋላ ሊመሰረቱ ይችላሉ። በተመሳሳይ መልኩ፣ ምንም እንኳን አቃቤ ሕግ በተጠርጣሪው የወንጀል የክስ መዝገብ ባይከፍትም፣ ተጠቂው ክስ የመክፈቻ ጊዜው እስካላለፈ ድረስ የፍትሃብሔር ክስ የመመስረት መብቱ የተጠበቀ ነው።

በፍትሃብሔር የክስ መዝገቦች ጊዜ፣ ተጠቂዎች ወንጀለኛው ግለሰብ ላደረሰባቸው ጥቃት ተጠያቂ ማድረግ ይችላሉ እና “ጉዳቶች” የሚባሉ ካሳ ሊጠይቁ ይችላሉ። የፍትሃብሔር የክስ መዝገብ የመክፈቻ የጊዜ ገደቦች፣ ስለዚህ ክስ መክፈት የሚፈልጉ ተጠቂዎች በተቻለ ፍጥነት ጠበቃ ማናገር ይችላሉ።

## የፍትሃብሔር ክስ ለመክፈት በሚወስኑበት ጊዜ መታየት ያለባቸው ጉዳዮች

ለወንጀል ተጠቂዎች የፍትሃብሔር ክስ መመስረት ሁልጊዜ የተሻለ አማራጭ ላይሆን ይችላል። የፍትሃብሔር ክስ ለመመስረት በመፈለግ ጊዜ አንድ ተጠቂ የሚከተሉትን ጉዳዮች ማጤን አለበት።

- ስዎች የፍትሃብሔር ክሶችን ሲመሰርቱ የሚያግዙ በጣም ጥቂት ነፃ የህግ ማማከር አገልግሎቶች አሉ። በአብዛኛው፣ ተጠቂው የፍትሃብሔር ክሱን ለመመስረት ጠበቃ መቅጠር ያስፈልገዋል፣ ይሄም በጣም ውድ ወጪ ይሆናል።
- የፍትሃብሔር ክሶች ስምንት ወራት ወይም ከዛ በላይ ሊወስድ ይችላል፣ እና ተጠቂው ከጠበቃ ጋር መገናኘት እና የፍርድ ቤት ችሎት ቆይታዎችን ጨምሮ ክሱን የሚመሰርትበት ጊዜ ያስፈልገዋል።
- የፍትሃብሔር ክስ ሂደቶች በአብዛኛው የሚከናወኑት በክፍት ችሎት ነው፣ ስለዚህ ተጠቂዎች በፍትሃብሔር ክስ ወቅት ሚስጥራቸውን እና የግል ጉዳያቸውን ሊያጡ ይችላሉ እና በችሎቱ ወቅት ቃላቸውን መስጠት ሊያስፈልጋቸው ይችላል።
- ምንም ኣንኳን አንድ የፍትሃብሔር ክስ ተጠቂው ቢያሸንፍም ከተከሳሹ የገንዘብ ካሳውን ለመውሰድ አሁንም ቢሆን ከባድ ሊሆን ይችላል።

## በወንጀለኛ ሕግ እና በፍትሃብሔር ላይ ያሉ ቁልፍ ልዩነቶች

### የወንጀል መቅጫ ህግ

- ዓላማው ተከሳሹን በማህበረሰቡ ላይ ላደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ማድረግ ነው።
- የመንግስት አቃቤ ሕግ ክሱን ይይዛል። ምንም እንኳን አቃቤ ሕጉ የተጠቂውን አስተያየት ቢቀበልም፣ ተጠቂው በፈለገው መልኩ የክስ መዝገቡ እንዲታይለት ማድረግ ላያስፈልገው ይችላል።
- አቃቤ ሕጉ ተከሳሹ ወንጀለኛ ስለመሆኑ በተጨማጭ ማስረጃ ያለምንም ጥርጥር ማስመስከር አለበት።
- ተከሳሹ ወንጀለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ተከሳሹ በእስር ሊታሰር ይችላል እና/ወይም የአመክሮ ጊዜ ሊገጥመው ይችላል። ፍርድ ቤቱ ከወንጀሉ ጋር በተያያዘ ለተጠቂው ወጪዎች ኣንዲከፍል ለተከሳሹ ካላዘዘ በስተቀር ተጠቂው ምንም ዓይነት የገንዘብ ካሣ አያገኝም።

## የፍትሃብሄር ክስ

- ዓላማው ተከሳሹ በተጠቂው ላይ ላደረሰው ወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ነው።
- ተጠቂው (“ከሳሽ ”) ክሱን የሚመሰርተው እና የሚከታተለው ራሱ ነው። የክሱ ወገን እንደመሆኑ መጠን፣ ወይም እንደ ክሱን የመሰረተ አንድሰው፣ ከሳሹ ከፍርድ ሂደቱ ጋር የተያያዙ ሁሉንም ሰነዶች መይዥ ይችላል እና እንደ የካሳ ስምምነት የመሳሰሉ የክሱ ጉዳዮች ላይ በተመለከተ ውሳኔ መስጠት ይችላል።
- ከሳሹ ተከሳሹ በሕግ ተጠያቂ እንደሆነ ማለትም ከዚያም በላይ በፍርድ ቤት ማረጋገጥ አለበት።
- ተከሳሹ ተጠያቂ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ተከሳሹ ለተጠቂው ላደረሰበት ጉዳት እና ችግር ካሣ መክፈል፣ ከወንጀሉ ጋር የተያያዙ ወጪዎች፣ እና ለፈጸመው ድርጊት ተከሳሹ ተጨማሪ የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይጠበቅበታል። ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን አንዳንድ እርምጃዎች እንዲያከናውን እና ለወደፊቱ ከተጠቂው እንዲርቅ ብያኔ ሊሰጥ ይችላል።

*ዝርዝሩ የተወሰደው ከዚህ ቀጥሎ በሚገኘው የናሽናል ሴንተር ፎር ቪክትምስ ኦፍ ክራይም ነው፡፡* victimsofcrime.org/ media/reporting-on-child-sexual-abuse/criminal-and-civil-justice.

## ሁለተኛ ተጠቂ ማለት ምንድን ነው?

ሁለተኛ ተጠቂ የሚያካትተው፥

- የተጠቂው ባለቤት፣ የወለዳቸው፣ የባላቤቱ ልጆች፣ በጉዲ ፈቻ የሚያሳድጋቸው፣ የልጅ ልጆች፡ ወላጆች፣ የባለቤት ወላጆች፣ ወንድሞችና እህቶች፣ የከፊል ወንድሞችና እህቶች፣ ወይም የባለቤት ወላጆች።
- ወንጀሉ ሲፈጸም ወይም ወንጀሉ ሲገኝ ጊዜ በተጠቂው መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖረው ግለሰብ።
- ከተጠቂው ሞት በኋላ የተወለደ የተጠቂው ልጅ ጨምሮ ሙሉለሙሉ ወይም በከፊል በተጠቂው ድጋፍ እና እንክብካቤ ጥገኛ የሆነ ከጥቃቱ የተረፈ ሰው።
- ከወንጀሉ ጋር በተያያዘ የሕክምና እና/ወይም የቀብር እና የማስቀበሪያ ወጪዎችን የሚሸፍን ግለሰብ።
- ከተጠቂው ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ሰው።
- ወንጀሉ ሲፈጸም የተመለከተ ሰው።

# የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የካሣ ፕሮግራም

የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የካሣ ፕሮግራም ለዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የወንጀሎቹን የገንዘብ ጉዳት ለመቀነስ የገንዘብ ድጋፍ ያቀርባል። ለግል ኢንሹራንስ ወይም ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ፕሮግራሞች ላይ የሚሸፈኑትን በማስወጣት ለተፈጸመባቸው ወንጀል በቀጥታ የሚመነጩ በተጠቂው ወይም በቤተሰቦች የተከፈሉ ወጪዎች ካሣ ይኖራቸዋል። ይሄ ፕሮግራም ለተጠቂው ጉዳት እና ችግር ወይም የግል ንብረት ውድመት ካሣ አይሰጥም።

ይሄ ክፍል የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የካሣ ፕሮግራም ጠቅላላ የብቁነት መስፈርቶችን መግለጫ ይሰጣል፥ ሆኖም ግን፣ እያንዳንዱ የካሣ ጥያቄ በተጠናጥል ይወስናል፣ እና ተጠቂው ወይም የተጠቂው ቤተሰቦች በጥያቄው ውስጥ የተካተቱን ሁሉንም ወጪዎች ሰነድ ማስገባት ያስፈልጋቸዋል።

## ለካሣ ክፍያ የብቁነት መስፈርቶች

ተጠቂዎች እና “ሁለተኛ ተጠቂዎች” ለካሳ ክፍያ ብቁ የሚሆኑት:

- በዲሲ ውስጥ በተፈጸመ የከፋ ወንጀል ሞት ወይም ጉዳት ከደረሰባቸው፣ ወይም በአሸባሪዎች ጥቃት የተነሳ ጉዳት ወይም ሞት የደረሰባቸው ወይም ከዩናይትድ ስቴትስ ውጪ የጅምላ ጥቃት ድርጊት የደረሰባቸው የዲሲ ነዋሪዎች፡
- ወንጀሉ ከተፈጸም በሰበት ቀናት ውስጥ ለሕግ አስከባሪዎች ወንጀሉ ሪፖርት ከተደረገ (ከታች ከተዘረዘሩት፣ አንዳንድ የሚታለፉ ጉዳዮች በስተቀር)፥
- የከሣ ክፍያ ማመልከቻው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከተሞላ ወይም ስለ ፕሮግራም በቅርቡ ያወቁ ከሆነ (መዘግየቱ ምክንያታዊ እንደሆነ ማሳየት ከቻሉ)፥
- ስለ ወንጀል ምርመራው ከሕግ አስከባሪዎች ጋር ትብብር ካደረጉ፥ እና
- በወንጀሉ ካልተሳተፉ፣ ካልተስማሙ፣ ወይም ወንጀሉን ካልቀሰቀሱ።

ምንም እንኳን ለሕግ አስከባሪዎች ወንጀሉ ሪፖርት ባያደርጉም አንዳንድ ተጠቂዎች የካሳ ክፍያውን ለመጠየቅ ብቁ ናቸው፥

- የወሲብ ጥቃት ምርመራ ያደረጉ ከሆነ የወሲብ ጥቃት ተጠቂዎች ብቁ ናቸው
- የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ የሚፈልጉ ከሆነ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች ብቁ ናቸው፥ እና
- የሕፃናት ላይ ጭቆና ተጠቂዎች ችላ እንደተባሉ ክስ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ ከተመሰረቱ ብቁ ናቸው።

## ለካሣ ክፍያ እንዴት እንደሚጠየቅ

በድህረገጽ dccourts.gov ላይ ወይም በዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚገኘውን ተጠቂዎች ማመልከቻ መሙላት አለባቸው። ይሄ ማመልከቻ እንዴት እንደሚሞላ ድጋፍ ለማግኘት ተጠቂዎች ተከራካሪያቸውን ወይም አቃቤ ሕጋቸውን ማግኘት አለባቸው። ማመልከቻዎች በአካል በመገኘት እዚህ ሊሞሉ ይችላሉ፡

**ዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሕንፃ A**
515 5th Street NW, Suite 109
Washington, DC 20001
202-879-4216
(የደብዳቤ ጥያቄዎችንም ይቀበላል)

**ዩናይትድ ሜዲካል ሴንትር (D.C. SAFE)**
1328 Southern Avenue SE, Room 311
Washington, DC 20032
202-561-3000

ጥያቄዎችን በፍጥነት በቶሎ እንዲመለሱ ሲባል ፣ እንደ የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዞች፣ እና ደረሰኞች ወይም የሒሳብ ማወራረጃ ሰነዶች የመሳሰሉትን ድጋፍ ሰጪ ማስረጃ ሰነዶችን ያቅርቡ።

የካሣ ጥያቄ መርማሪዎች ፖሊስን፣ የተጠቂውን ቀጣሪ፣ ተጠቂው ሕክምና ያገኘበትን ሆስፒታል፣ እና/ወይም ሌሎች ተዛማጅ ኤጀንሲዎች ወይም ድርጅቶችን በማግኘት በማመልከቻው ላይ ስለቀረቡት መረጃዎችን ያረጋግጣሉ። ስለ የካሳ ክፍያ መርማሪው ውሳኔ ተጠቂው በደብዳቤ ምላሽ ይሰጠዋል።

## የካሣ ክፍያ ላይ የይግባኝ ጥያቄ ማቅረብ

የከሣ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ፣ ወይም ከተጠየቀው የገንዘብ መጠን በታች ከሆነ፣ ተጠቂዎች ድጋፍ ለማግኘት እና የይግባኝ ጥያቄ ማንሳት የሚቻል መሆኑን ለመጠየቅ ተከራካሪያቸውን ማግኘት አለባቸው ። የካሣ ጥያቄው ተቀባይነቱ ካጣ በኋላ በ 30 ቀናት ውስጥ ክሱን በተመለከተ አዲስ መረጃ የተገኘ ከሆነ፣ ተጠቂዎች "በድጋሚ ይታይልኝ ጥያቄ" ማስገባት ይችላሉ።

---

## የካሣ ዓይነቶች

ከታች ለተጠቀሱት ነገሮች ተጠቂዎች እና ሁለተኛ ተጠቂዎች ካሣ መጠየቅ ይችላሉ። ለእያንዳንድ የካሳ ጥያቄ እስከ $25,000 ዶላር ድረስ መጠየቅ ይቻላል። እነዚህ የገንዘብ መጠኖች ከሴምፕቴምበር 2017 ጀምሮ ትክክለኛ ናቸው፡ የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የካሣ አከፋፈል ፕሮግራም በዚህ ድረገጽ ላይ ይጎብኙ

dccourts.gov for updates.

### የሕክምና ወጪዎች

የአካል፣ የአዕምሮ ቴራፒ ሕክምና፣ ወይም የመልሶ ማገገሚያ ያካትታል።

### የአዕምሮ ጤና ሕክምና
ለአዋቂዎች እስከ $3,000፥ ለሕፃናት እስከ $6,000 (እንዲሁም ለሁለተኛ ተጠቂዎች)።

### የታጣ ደሞዝ
ካሳ የ 52 ሳምንታት ወይም $10,000 ድረስ ያልበለጠ መሆን አለበት።

### ለጥገኞች ድጋፍ ሰጪ ማጣት
ተጠቂው በሚሞትበት ሰዓት እና ሶሻል ሴኩሪቲ ተቀባይነት ሲያጣ፣ በአንድ ጥገኛ እስከ $2,500 ዶላር፣ በአንድ ጥቃት ከ $7,500 በላይ መብለጥ የለበትም።

### የቀብር ስነስርዓት ወጪዎች
እስከ $6,000 ዶላር ድረስ።

### ወንጀል የፈጸመበት ቦታ ማጽጂያ
እስከ $1,000 ዶላር ድረስ።

### በፖሊስ እንደ ማስረጃ የተያዘ ልብስ መቀየሪያ
እስከ $100 ዶላር ድረስ፥ ተጠቂው የሞተ ከሆነ አይሰጥም።

### ጊዜያዊ ምግብ እና የቤት መጠለያ
በወንጀሉ የተነሳ አስፈላጊነቱ የግድ ከሆነ፥ 120 ቀናት ያልበለጠ እስከ የመጨረሻ $400 ዶላር ለምግብ ወጪዎች እና $3,000 ዶላር ለመኖሪያ ቤት።

### የመንቀሳቀሻ ወጪዎች
እስከ $1,500 ዶላር ድረስ፥ በተጠቂው ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ በመውደቁ የተነሳ ቦታ መቀየር ግዴታ ከሆነ የሚሰጠው ወንጀሉ ከተፈጸመ 120 ቀናት ውስጥ ብቻ ነው።

### የትራንስፖርት ወጪዎች
ለስቴት ውስጥ መጓጓዣ እስከ $100 ዶላር እና ከስቴት ውጪ ለሆነ መጓጓዣ እስከ $500 ዶላር ውስጥ ነው። ይሄ ወጪ የሚውለው በምርመራ ውስጥ ለመሳተፍ ወይም በችሎት ጊዜ ነው፣ ወይም የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት፣ ወይም በወንጀሉ የተነሳ ሌሎች አንዳንድ አስፈላጊ ወጪዎችን ለመሸፈን ነው።

### የበር፣ የመስኮት፣ የቁልፍ ወይም የተጠቂውን መኖሪያ ቤት ጥበቃ ለማጠናከር የሚወጡ ወጪዎች
እስከ $1,000 ዶላር ድረስ።

### የጠበቃዎች ክፍያ
ይሄ የሚሰጠው በይግባኝ ጊዜ ለሚወሰነው ሲሆን፥ ከ $500 ዶላር ያልበለጠ ወይም ከካሳው 10 ፐርሰንት በላይ ያልበለጠ ወይም ከዛ ያነሰ ነው።

### የድንገተኛ ካሣ
እስከ $1,000 ዶላር ድረስ።

# ለቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች መረጃ

ይሄ ክፍል የሚያካትተው የቤት ውስጥ ጥቃት ለደረሰባቸው የተወሰኑ የዲሲ ተጠቂዎች ለማገዝ ነው። ምንም እንኳን አጥቂው ላይ የፖሊስ ሪፖርት ለማድረግ ባይፈልጉም የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ሰላም የመነሳት፣ ወይም ትንኮሳ ለሚያጋጥማቸው ስዎች ልዩ ግብአቶች አሉ።

በዲሲ ህግ መሰረት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት የሚያካትተው "የቅርብ የፍቅር ጓደኛ ጥቃት" እና "**በቤተሰብ መካከል የሚደረግ ጥቃት**" ናቸው።

> **የቅርብ የፍቅር ጓደኛ ጥቃት** ማለት አንድ ግለሰብ በትዳር አጋሩ ላይ፣ የቤት ውስጥ የፍቅር ጓደኛ፣ ወይም በፍቅር ግንኙነት ያለው ሰው ላይ፣ በፍቅር እያየው ያለ ሰው፣ ወይም የወሲብ ግንኙነት ያለው ሰው ላይ ወንጀል ሲፈጸም ወይም ለመፈጸም ዛቻ ሲደርስ ነው።
>
> **በቤተሰብ መካከል የሚደረግ ጥቃት** ማለት አንድ ሰው በደም ከተሳሰረው፣ በጉዲፈቻ፣ በሕግ ጥበቃ፣ በትዳር፣ ወይም የቤት ውስጥ አብሮ ከሚኖረው፣ ልጅ ካስወለዱት ግለሰብ ላይ ወንጀል ሲፈጸም ወይም ዛቻ ሲደርስ ነው።

## ፈጣን ድጋፍ

ለፈጣን ወይም ለድንገተኛ የፖሊስ እና የሕክምና ድጋፍ ለማግኘት፣ 911 ላይ ይደውሉ። ለፖሊስ መደወል የማይፈልጉ ከሆነ ነገር ግን አስቸኳይ ድጋፍ ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፣ የዲሲ ተጠቂዎች የነፃ የስልክ መስመር ላይ በ 1-844-4-HELPDC (1-844-443-5732) ላይ ይደውሉ። የድንገተኛ ጊዜ መጠለያን ጨምሮ፣ ሊኖሮት የሚችለውን አማራጮች ሊያስረዳዎት ከሚችል ተከራካሪ ጋር ፖሊሱ ወይም በነፃ ስልክ ኦፕሬተሩ ሊያገናኝዎት ይችላል።

የቤት ውስጥ ጥቃት መመዝገቢያ ማዕከል የማማከር፣ የደህንነት ዕቅድ ጨምሮ ለዲሲ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች ሁሉን አቀፍ ድጋፍ፥
እና የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ የፍርድ ቤት ማዘዣዎችን ማውጣት ላይ እገዛ ይሰጣል። በዲሲ የመንግስት ኤጀንሲዎች እና ለትርፍ ያልቆሙ ድርጅቶች መካከል ያለ ትብብር ውጤት የሆነው የቤት ውስጥ ጥቃት መመዝገቢያ ማዕከል ሁለት ቦታዎች ላይ ይሰራሉ፡ የዲሲ ከፍተኛ የፍርድ ቤት እና ዩናይትድ ሜዲካል ማዕከል። የሁለቱም ቦታዎች መረጃ ሰጪ እና የአገልግሎት ዝርዝርን ለማግኘት በገጽ 47 ላይ በመሄድ ይመለከቱ።

## የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ (CPO) ማግኘት

ብዙ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች እንደ መጀመሪያ ደረጃ አካሄድ የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ለማግኘት ይመርጣሉ ምክንያቱም ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ሳያስፈልግ ስለሚወጣ ወይም የወንጀል ክስ ሂደቶችን መከተል ስለማያስፈልግ። የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የዲሲ ተጠቂዎች የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ማውጣት ላይ የሚያግዛቸውን ተከራካሪ ጋር እንዲገናኙ ነፃ የስልክ መስመር በ 1-844-4-HELPDC (1-844-443-5732) ላይ መደወል አለባቸው። በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ስላሉት ሦስት የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ዓይነቶች መረጃ ከታች ማብራሪያ ይገኛል። የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ በወንጀለኛ ፍርድ ቤት ውስጥ ለተከሳሽ በዳኛዎች ከሚወሰነው የወንጀለኛ “ርቀት ጠብቅ ትዕዛዝ” የተለየ ነው። ስለ ርቀት ጠብቅ ትዕዛዞች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ገጽ 11 ላይ ይመልከቱ። የወሲብ ጥቃት ለደረሰባቸው ለኮሌጅ ትምህርት ተማሪዎች የተለያዩ እራስን ከጥቃት መጠበቂያ ዘዴዎች ይኖራሉ። ስለእነዚህ ጥበቃዎች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ተማሪዎች የራሳቸውን ዩኒቨርሲቲ ማነጋገር አላባቸው።

## የፍትሃብሄር ጥበቃ ትዕዛዝ ዓይነቶች

### ጊዜያዊ የጥበቃ ትዕዛዝ (TPO)

ይሄ የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ እንዲወጣ ለፍርድ ቤት የማዛዣ ጥያቄ ከቀረበ በኋላ እና የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ መሰጠት እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ዳኛው በችሎት ከመወሰኑ በፊት ለመሸጋገሪያ ጊዜ የሚወጣ የፍርድ ቤት ጥበቃ ትዕዛዝ ነው። የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ የሚሻ ማንኛውም ተጠቂ ለሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ የማውጫ ጥያቄ ለፍርድ ቤት በቀረበበት ተመሳሳይ ቀን ላይ የጊዜያዊ ጥበቃ ትዕዛዝ ይወጣል።

### የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ (CPO)

ይሄ በዳኛው የተፈረመበት፣ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ግለሰቡ ተጠቂውን ማስፈራራቱን፣ መጠጋቱን እና ለማዋራት መሞከሩን እንዲያቆም የሚያዝ፣ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ነው። ይሄንን ትዕዛዝ መጣስ በፍርድ ቤት ውስጥ እንደ ከፍተኛ የወንጀል ድርጊት ይቆጠራል። የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል እና መደበኛው የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዙ ከማለቁ በፊት ተጠቂው ኣንዲራዘም የሚጠይቅ ከሆነ ለሌላ ተጨማሪ ዓመት ሊራዘም ይችላል።

### የድንገተኛ ጊዜያዊ ጥበቃ ትዕዛዝ

ይሄ ከመደበኛው የፍርድ ቤት የሥራ ሰዓት ውጪ ተጠጊው አስጊ ሁኔታ ውስጥ በሚገኝበት ወቅት የሚወጣ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ነው። ይሄ ትዕዛዝ ለአምስት ቀናት ያህል ይቆያል እና በዲሲ ሴፍ በኩል መጠየቅ አለበት። ይሄ ሂደት ኤምፒዲ እና ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ አቃቤ ሕግን ያሳትፋል።

---

የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ለማግኘት፣ በዲሲ የከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በደቡብ ምስራቅ ዲሲ አካባቢ የሚገኘው ዩናይትድ ሜዲካል ማዕከል ውስጥ ቢሮ ያለው የቤት ውስጥ ጥቃት መመዝገቢያ ማዕከል ላይ ተጠቂው የማዛዣ ወረቀት የማውጣት ክስ መመስረት አለብት። ለበለጠ መረጃ ለማግኘት ገጽ 30 እና 47 ላይ ይመልከቱ። ከፍርድ ቤት ማዘዣ ወረቀት ማውጣት እና ጥበቃ ትዕዛዝ እንዲሰጠው የተፈለገው ግለሰብ ("ምላሽ ሰጪው") ላይ የፍርድ ቤት ማዛዣ ወረቀቱን እንዴት እንደሚሰጥ ያሉትን አማራጮች ለመወያየት ድጋፍ የሚሰጡ የተጠቂ ተከራካሪዎች አሉ። ስለ ችሎቱ የመጥሪያ ወረቀት ለምላሽ ሰጪው በሚገባ በ 14 ቀናት ውስጥ (የጊዜ ማራዘሚያ ካልተሰጠ በስተቀር) ካልቀረበ በስተቀር የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ማዘዣው አይወጣም። ምላሽ ሰጪው የታቀደው ትዕዛዝ ላይ ከተስማማ፣ ዳኛው ትዕዛዙን ያወጣል። ምላሽ ሰጪው የማይስማማ ከሆነ፣ የማዛዣ ወረቀቱ ይውጣ ወይም አይውጣ የሚለውን የሚወሰነው ዳኛው ፊት ጉዳዩ ለችሎት ይቀርባል። የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዙን ዳኛው የማይሰጥ ከሆነ፣ ተጠቂው የፍርድ ቤት መዝገብ ያዥን ማነጋገር ወይም ለተጨማሪ አማራጮች በ 1-844-4-HELPDC (1-844-443-5732) ላይ መደወል አለባቸው።

## የፍትሃብሄር ጥበቃ ትዕዛዝ በሚወጣበት ሰዓት፣ ዳኛው ሊያዝ የሚችለው ግለሰቡ ከ:

- ጥቃት ማድረሱን እንዲያቆም (ተጠቂውን መጉዳት እና ማስፈራራት ጨምሮ)፥
- ከተጠቂው ወይም ከልጆቻቸው (ጊዜያዊ የልጆች ጥበቃ ለተጠቂው ሊወሰን ይችላል) እንዲርቅ፥
- በጋራ ከሚኖሩበት ቤት ውስጥ እንዲወጡ፥
- በማንኛውም ዓይነት መንገድ ተጠቂውን ለማግኘት እንዲያቆም፥
- ለእፅ መጠቀም ወይም ንዴትን መቆጣጠር ላይ የምክር አገልግሎት እንዲወስድ፥
- የጦር መሳሪያዎችን እንዲያስረክብ፥ ወይም
- ከሁኔታው ጋር የሚገናኝ ማንኛውም ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያከብር።

## አንድ ሰው የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝን የሚጥስ ከሆነ?

ማወኩን፣ መጎንተሉን ወይም ተጠቂውን ማጥቃቱን ከቀጠለ፣ ወይም የትዕዛዙ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውንም አንቀጽ የጣሰ እንደሆነ ምላሽ ሰጪ፣ የወንጀል ድርጊት የሆነውን፣ ከፍርድ ቤት የወጣ ትዕዛዝን አያከበረ አይደለም። የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝን ምላሽ ሰጪው የጣሰ እንደሆነ፣ ተጠቂው ለፖሊስ ደውሎ እና/ወይም ለፍርድ ቤቱ የወንጀል መጣስ ድርጊት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል። ወይ የዩኤስ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ አቃቤ ሕግ ቢሮ አልያም ደግሞ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ አቃቤ ሕግ ቢሮ ጥሰቱን ለፍርድ ሂደት ያቀርባል። ጉዳዩን በፍርድ ቤት ውስጥ ለማቅረብ የመረጡ እንደሆነ፣ ስለ ክስ መዝገቡ ለመወያየት ከእነዚህ ቢሮዎች ውስጥ ከሚገኙ ጠበቆች አንዱ ተጠቂውን ያናግረዋል። አንዳንድ ጊዜ ላይ ምላሽ ሰጪው ያነሰ የፍርድ ቅጣት ለማግኘት ጥፋቱን የሚያምንበት የጥፋተና ነኝ ስምምነትን በመስማማት ክሱ መፍትሔ ሊቋጭ ይችላል። በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ የክስ መዝገቦቹ እንደ ወንጀል ያታዩና በችሎት ውስጥ ውሳኔ ያገኛሉ። ተጠቂው ችሎቱ ውስጥ ቃሉን እንዲሰጥ ሊፈለግ ይችላል፣ በዚህ ጊዜ ተጠቂው እንዴት ምስክር መስጠት እንዳለበት ለማዘጋጀት አቃቤ ሕጉ ከተጠቂው ጋር አስቀድሞ ይገናኛል።

**ማዛዣ ጠያቂ**
የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ያስፈለገው ግለሰብ

**ምላሽ ሰጪ**
ማዛዣ እንዲወጣ የጠየቀው ግልሰብ ማዛዣው እንዲሰጠው የፈለገው ግለሰብ።

## በተጠቂው መኖሪያ ቤት ውስጥ የደህንነት ጉዳዮች

የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች ቁልፋቸውን እንዲቀይሩላቸው ለቤት አከራዮቻቸው የጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ እና ከወንጀሉ በኋላ በቤታቸው ውስጥ መኖር ደህንነት የማይሰማቸው ከሆነ ከዲሲ አፓርትመንት ጋር ያላቸውን የሊዝ ኮንትራንት ማቋረጥ ይችላሉ። የሊዝ ኮንትራት ለማቋረጥ፣ ተጠቂዎች የሊዝ ኮንትራቱን በቤት ውስጥ ጥቃት የተነሳ በ 14 ቀናት ውስጥ እንደሚያቋርጡ የሚገልጽ ደብዳቤ ለቤት አከራዩ መስጠት አለባቸው። ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተከራዩ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከተጠቂው ተከራካሪ፣ የፖሊስ መኮንን፣ ዶክተር፣ ወይም የዲስ የቤቶች ባለስልጣን ተወካይ ዓባሪ የሚደረግ ደብዳቤ ይያያዛል፣ ወይም ተጠቂው አግኝቶት ከሆነ የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ቅጂው ይያያዛል።

## ለቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች የገንዘብ ድጋፍ

የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች በደረሰባቸው ጥቃት የተነሳ ያልተጠበቁ የገንዘብ ወጪዎችን ሊያወጡ ይችላሉ። ምንም እንካን እንደዚህ ዓይነት ካሣዎች ዋስትናቸው ያልተጠበቀ ቢሆንም፣ ፕሮግራሙን በሚያስተዳድረው የዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንዳንድ ነገሮች እና የገንዘብ መጠኑ የሚወሰን ቢሆንም፣ ተጠቂዎች ዲስ የወንጀል ጥቃት የካሣ አከፋፈል ፕሮግራም ላይ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ምንም እንኳን ለፖሊስ ወንጀሉን ሪፖርት ለማድረግ ባይሞክሩም የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ የሚሹ ተጠቂዎች እነዚህን ገንዘቦች ማግኘት ይችላሉ። ስለ ዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የካሣ ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ ገጽ 25 ላይ በመሄድ ይመልከቱ።

የዲሲ ቴምፖራሪ አሲስታንስ ፎር ኒዲ ፋሚሊስ (TANF) ፕሮግራም ጥቅማጥቅሞችን የሚቀበሉ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች ከ TANF የሥራ መስፈርት እፎይታን ማግኘት ጨምሮ፣ ሥራ ዕድል እና ሃላፊነት (POWER) ፕሮግራም በኩል የሚሰጡትን ልዩ አገልግሎቶችን እና ግብአቶችን ለማግኘት ብቁ ናቸው።

ለበለጠ መረጃ፣ የ dhs.dc.gov/page/benefits-dhs ድህረ ገጽ ይጎብኙ ወይም ዲፓርትመንት ኦፍ ሁማን ሰርቪስን በ dhs@dc.govላይ ያግኙ ወይም 202-671-4200 (711 for TTY) ላይ ይደውሉ።

### ጠቃሚ መረጃ

አጥቂዎን ለመሸሽ የሚፈልጉ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂ ከሆኑ፣ ለቤት እንስሳቶችዎ ነፃ የድንገተኛ ጊዜ የማቆያ ቦታ ይገኛል። የሁማን ሪሶርስ አልያንስን በ 202-723-5730 ላይ ደውለው ያግኙና ስለ ሴፍ ሔቨን ፕሮግራም ይጠይቁ ወይም ደግሞ ይሄንን ይጎብኙ www.humanerescuealliance.org/domestic-violence-support.

# ግብአቶች


የፍትሕ መስጫ አደባባይ ካርታ ..... 36

ለፍርድ ቤቶች እና የመንግስት ተቋማት የማግኛ አድራሻ ..... 37

ለጅማሬ ያህል ..... 49

D.C. የወንጀል ፍትሕ አሰጣጥ ካርታ ..... 50

የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች ..... 52

የቃላት መፍቻ ..... 59

የክስ መመዝገቢያ ..... 64


በግብአቶች ክፍል ላይ ያለው መረጃ ከሴፕቴምበር 2017 ጀምሮ ትክክለኛ ነው። የተሻሻለ መረጃ የሚገኝ ከሆነ፣ የኮውንስል ኦፍ ኮርት ኤክሰለንስ (CCE) የ *የተጠቂዎች መመርያን* ያሻሽላል።

ይሄንን መለያ በፒዲኤፍ የፋይል ቅርጸት እዚህ ያውርዱ courtexcellence.org/digital-library.

የዚህን መመሪያ የመስመር ላይ (የድህረ ገጽ) ስሪት ለማግኘት victimsguide.courtexcellence.org ላይ ይሂዱ።

## የፍርድ ቤቱ መንገድ ካርታ

የዲሲ ፍርድ ቤቶች እና አቃቤ ሕግ እና የሕዝብ ተቆርቋሪ ቢሮዎች የሚገኙት በሕዝብ ትራንስፖርት የሚገኘ የጁዲሻሪ አደባባይ ላይ ነው። በሬድ ላይን ላይ የሆነው የጁዲሻሪ አደባባይ ባቡር ጣቢያ ላይ ሁለት መግቢያዎች አሉት።



# የፍርድ ቤቶች እና የመንግስት ኤጀንሲዎች መገኛ አድራሻ

## የአካባቢው ፖሊስ – ሜትሮፖሊቲያን ፖሊስ መመሪያ (MPD)

**ዋና መስሪያቤቶች**
300 Indiana Avenue NW, Room 5059
202-727-9099
711 | TTY
mpd@dc.gov
mpdc.dc.gov

**የመጀመሪያ ዲስትሪክት**
101 M Street SW
202-698-0555
202-727-8506 | TTY

**ሁለተኛ ዲስትሪክት**
3320 Idaho Avenue NW
202-715-7300
202-364-3961 | TTY

**ሦስተኛ ዲስትሪክት**
1620 V Street NW
202-673-6815
202-518-0008 | TTY

**አራተኛ ዲስትሪክት**
6001 Georgia Avenue NW
202-715-7400
202-722-1791 | TTY

**አምስተኛ ዲስትሪክት**
1805 Bladensburg Road NE
202-698-0150
202-727-5437 | TTY

**ስድስተኛ ዲስትሪክት**
5002 Hayes Street NE
202-698-0880
202-398-5397 | TTY

**ሰባተኛ ዲስትሪክት**
2455 Alabama Avenue SE
202-698-1500
202-889-3574 | TTY

**በድንገተኛ ጊዜ፣ ሁልጊዜ ላይ ይደውሉ። ድንገተኛ ላልሆኑ የፖሊስ እና የሌሎች የመንግስት አገልግሎቶችን ለማግኘት 311 ላይ ይደውሉ ወይም 311.dc.gov ይጎብኙ።**

ኤምፒዲ ዋና መስሪያ ቤቶች እና የዲስትሪክት ጣቢያዎች ለሕዝብ በቀን 24 ሰዓት፣ በዓመት 365 ቀናት ክፍት ናቸው። ለድንገተኛ ያልሆኑ፣ የዲስትሪክት ጣቢያዎች ላይ መደወል ይችላሉ። በሚደውሉበት ጊዜ አንድ ሰው ወዲያውኑ መልስ የማይሰጥ ከሆነ፣ በ 24 ሰዓታት ውስጥ መልዕክቱን ይልካል። ስለ ኤምፒዲ ቢሮዎች የበለጠ መረጃ ለማግኘት በዚህ ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ mpdc.dc.gov.

## ስፔሻላይዝድ ኤምፒዲ ዩኒትስ

ስለ ስፔሻላይዝድ ኤሜፒዲ ዩኒቶች የተሟላ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን mpdc.dc.gov/page/specialized-units ይጎብኙ።

**የኤዥያ ሊያሶን ዩኒት (ALU)**

202-535-2653
202-347-8164 | TTY
asian.liaison@dc.gov
mpdc.dc.gov/page/asian-liaison-unit

ኤኤልዩ (ALU) ለኤሽያ ማህበረሰብ የሕዝብ ደህንነት ፍላጎት ላይ የሚያተኩሩ ለዚህ ዓላማ የተዘጋጁ የመኮንኖች ቡድን ነው።

**የመስማት የተሳናቸው እና ማዳመጥ የሚያቅታቸው ሊያዞን ዩኒት (DHHU)**

202-553-7874
202-347-8164 | TTY
mpd.dhhu@dc.gov
mpdc.dc.gov/node/139002

DHHU መስማት ለተሳናቸው እና ማዳመጥ ለሚያቅታቸው ማህበረሰቦች የህዝብ ደህንነት ፍላጎት ላይ የሚያተኩሩ ለዚህ ዓላማ የተዘጋጁ መኮንኖች ቡድን ነው።

**የቤት ውስጥ ጥቃት ዩኒት**

202-727-7137
mpdc.dc.gov/page/domestic-violence-unit

የቤት ውስጥ ጥቃት ዩኒት በኤምፒዲ፣ በዩኤስ አቃቤ ሕግ ቢሮ፣ በሌሎች የሕግ አስከባሪ ድርጅቶች፣ የተጠቂ አገልግሎት ኤጀንሲዎች፣ የተጠቂ ተከራካሪዎች፣ እና በማህበረሰቡ መካከል እንደ ሊያዞን ሆኖ ይሰራል።

**ላቲኖ ሊያዘን ዩኒት / La Unidad de Enlace Latino (LLU)**

202-673-4445
202-347-8164 | TTY
unidadenlace.latino@dc.gov
mpdc.dc.gov/page/latino-liaison-unit

ኤል ኤል ዩ (LLU) የላቲኖ ማህበረሰብን የሕዝብ ድህንነት ፍላጎቶች ላይ የሚያተኩሩ ለዚህ ዓላማ የተዘጋጁ የመኮንኖች ዩኒት ነው።

La Unidad de Enlace Latino fue creada para ayudar a la comunidad latina y para aumentar la confianza y comunicación que existe entre la comunidad latina y MPD.

**የሌዚቢያን፣ ጌይ፣ እና ትራንጀንደር ሊያዞን ዩኒት (LGBTLU)**

202-506-0714
202-347-8164 | TTY
mpdc.dc.gov/node/139172

LGBTLU የጌይ፣ ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል፣ እና ትራንስጄንደር ኮምዩኒቲ እና የእነሱ ተባባሪዎች የሕዝብ ደህንነት ፍላጎት ላይ የሚያተኩሩ ለዚህ ዓላማ የተዘጋጁ መኮንኖች ቡድን ነው።

**የወሲብ ጥቃት ዩኒት**

202-727-3700
mpdc.dc.gov/page/sex-assault-unit

የኤምፒዲ የወሲብ ጥቃት ቡድን ዕድሚያቸው 18 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የወሲብ ጥቃት ይመረምራል። ታዳጊ ወጣቶችን የሚመለከት የወሲብ ጥቃቶች ምርመራ የሚደረግባቸው በወጣቶች እና ቤተሰብ አገልግሎቶች ዲቪዚዮን ነው። የኤሞኢዲ ተጠቂ አገልግሎቶች ዩኒት የተጠቂ ስፔሻሊስቶች በምርመራው ጊዜ መረጃ፣ ድጋፍ፣ ለወሲብ ጥቃት ተጠቂዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ሪፈራል ለማቅረብ ከወሲብ ጥቃት ዩኒት መርማሪዎች ጋር አብረው በመሆን በጋራ ይሰራሉ።

**የተጠቂዎች አገልግሎቶች ቅርንጫፍ**

202-724-4339
mpdc.dc.gov/page/ victim-services-branch

የኤምፒዲ ተጠቂ አገልግሎቶች ቅርንጫፍ ድጋፍ፣ መረጃ፣ እና ለተጠቂዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ሪፈራሎችን ያቀርባል፥ የቤተሰብ ሊያዞን ስፔሻሊስት ዩኒት (FLSU)፣ የዋና ክስ ተጠቂዎች ዩኒት (MCVU)፣ እና የተጠቂ ስፔሻሊስት ዩኒት (VSU) ያካትታል።

**ወጣቶች እና የቤተሰብ አገልግሎቶች ዲቪዚዮን (YFSD)**

202-576-6768
mpdc.dc.gov/page/
youth-and-family-services-division

YFSD ከሌሎች ጉዳዮች መካከል የልጆን ጥቃት እና ችላ መባልን፣ የልጆች የወሲብ ጥቃት እና ብዝበዛ፣ እና የታዳጊ ወጣቶች የጠፉ ሰዎችን ፍላጋ እና የቤተሰብ ማገትን ምርመራ ለማድረግ ሃላፊነት ተሰጥቶታል። እንደዚሁም በዲሲ ውስጥ ሁሉንም የታሰሩ ታዳጊ ወጣቶች ሂደት ያስፈጽማል።

## ሌሎች የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎችን ይምረጡ

**ሜትሮ ትራንዚት የፖሊስ ዲፓርትመንት**
የዋሽንግተን ሜትሮፖሊቲያን አካባቢ ትራንዚት ባላስልጣን
600 5th Street NW
Washington, DC 20001

202-962-2121 | 24-ሰዓት
MyMTPD (696783) | በጽሁፍ መልዕክት
301-955-5000 | የወንጀል ምርመራ ዩኒት

wmata.com/about/transit-police/ contact-us.cfm

ሜትሮ ትራንዚት ፖሊስ በዲሲ፣ ሜሪላንድ እና ቨርጂኒያ ሜትሮ ፋሲሊቲዎች፣ አውቶብሶች፣ እና ባቡሮች ውስጥ ለተከሰቱ ወንጀሎች የመቆጣጠር ስልጣን አለው።

**የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል ፖሊስ**
119 D Street NE Washington, DC 20510

202-224-5151 | የተጠቂ ምስክር ድጋፍ ሰጪ 202-224-5151 | ድንገተኛ ያልሆነ (24 ሰዓታት) 202-224-1677 | የሕዝብ መረጃ ቢሮ

ይጠይቁUSCP@uscp.gov
uscp.gov

የዩኤስ ካፒቶል ፖሊስ በዩኤስ ካፒቶል መሬቶች ላይ ለተፈጸሙ ወንጀሎች የመቆጣጠር ስልጣን አለው።

**የዩናይትድ ስቴትስ ፓርክ ፖሊስ**
የወንጀል ምርመራ ቅርንጫፍ (CIB)
1901 አናኮስቲያ ድራይቭ ኤስ ኢ ዋሽንግተን ዲሲ 20019

202-610-8730 | CIB
202-610-7500 | 24-ሰዓት ድንገተኛ
202-610-7505 | 24-ሰዓት ድንገተኛ ያልሆነ
202-439-1808 | መዝገቦች

nps.gov/subjects/uspp/index.htm

የዩኤስ ፓርክ ፖሊስ የናሽናል ሞልን ጨምሮ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ የሚገኙ በማንኛውም ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ የሚከሰቱ ወንጀሎች ላይ የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት።

## የአቃቤ ሕግ ኤጀንሲዎች

**ኦፊስ ኦፍ ዘ አተርኒ ጀነራል ፎር ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ**
የተጠቂዎች ምስክሮች ድጋፍ ዩኒት 441 4th Street NW Washington, DC 20001

202-727-3400
202-727-3400 | TTY

dc.oag@dc.gov oag.dc.gov/page/victim-witness- assistance-unit

የስራ ሰዓት: ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30 a.m. እስከ 5 p.m.

ዘ ኦፊስ ኦፍ ዘ አተርኒ ጀናል ኦፍ ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ (OAG)
ከተወሰኑ ሌሎች የአዋቂ ወንጀል ፈፃሚዎች ጋር በታዳጊ ወጣት የፍትሕ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ ለፍርድ የሚቀርቡ የወንጀል ጥሰቶችን ለፍርድ ያቀርባል። የ OAG የተጠቂ ምስክር
OAG ወንጀለኛውን ለፍርድ በሚያቀርብበት ወቅት ለከፋ ወንጀል ተጠቂዎች የድጋፍ ሰጪው ዩኒት የድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል።

**ዩኤስ አተርኒ ኦፊስ ፎር ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ**
የተጠቂዎች ምስክር ድጋፍ ሰጪ ዩኒት 555 4th Street NW, Suite 1412
Washington, DC 20530

202-252-7130
202-305-9195 | TTY

justice.gov/usao-dc/ victim-witness-assistance

የስራ ሰዓት: ሰኞ እስከ አርብ፣ 8 a.m. እስከ 5 p.m.

የዩኤስ አተርኒ ኦፊስ ፎር ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ (USAO-DC) አብዛኛዎቹን የዲስ ወንጀሎችን ለፍርድ የሚያቀርብ የፌደራል ኤጀንሲ ነው። USAO-DC የተጠቂ ምስክር ዩኒት በፍርድ ቤት ውስጥ ማጀብ፣ የደህንነት ዕቅድ፣ የምስክር ደህንነት ግምገማ፣ ከከተማ ውጪ ላሉ ተጠቂዎች የጉዞ እና የመጠለያ ማመቻቸት፣ የስሜት ድጋፍ እና የችግር ጊዜ ድጋፍ፣ የማሳወቅ አገልግሎት፣ እና ለማማከር አገልግሎት ሪፈራል መስጠት፣ የቤት አገልግሎት፣ የትራንስፖርት፣ የወንጀል ተጠቂዎች ካሣ፣ እና የሕክምና ወይም የአዕምሮ ጤና ፍላጎቶችን ማሟላት ጨምሮ ለተጠቂዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እና አገዛ ይሰጣል።

## የሕዝብ ተከራካሪዎች

**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ተከራካሪ አገልግሎት (ዋና ቢሮ)**
633 Indiana Avenue NW Washington, DC 20004

202-628-1200
1-800-341-2582 | ከፍያ ነፃ ጥሪ
202-824-2531 | TTY

pdsdc.org

የስራ ሰዓት: ከሰኞ እስከ አርብ፣ 9 a.m. እስከ 5:30 p.m.

ይሄ ቢሮ ጠበቃ መቅጠር የማይችሉ በወንጀል ለተከሰሱ ሰዎችን ጥብቅና ይቆማል።

**ኦፊስ ኦፍ ዘ ፌደራል ፐብሊክ ዲፌንደር ፎር ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ**
625 Indiana Avenue NW
Washington, DC 20004

202-208-7500

dc.fd.org

የስራ ሰዓት: ሰኞ እስከ አርብ፣ 9 a.m. እስከ 5 p.m.

ይሄ ቢሮ በፌደራል ወንጀል ተከሰው ጠበቃ መቅጠር ለማይችሉ ግለሰቦች ጥብቅና ይቆማል።

## የችሎት ፍርድ ቤቶች

**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ**
**ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

H. Carl Moultrie Courthouse 500 Indiana Avenue NW Washington, DC 20001

202-879-1400

dccourts.gov/superior-court

የስራ ሰዓት: ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30 a.m. እስከ 5 p.m.

የዲስ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከዲሲ ሕግ ጋር በተያያዘ የፍትሃብሔር እና የወንጀል ጉዳዮችን ይመለከታል። የወንጀል ክሶች በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የወንጀል ዲቪዚዮን፣ በቤተሰብ ችሎት፣ ወይም በቤት ውስት ጥቃት

ዩኒት ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ። በፍርድ ቤት መግቢያ ላይ ያሉ መዝገብ ቤት ሠራተኞች እና የወንጀል መረጃ ማዕከል ሠራተኞች (በአራተኛው ወለል ላይ በክፍል ቁጥር 4001 ላይ የሚገኘው) ስለ አንድ ችሎት ሰዓት እና አካባቢ መረጃ ሊያቀርቡ ይችላሉ እና ለፍርድ ቤት መመሪያ ሊሰጡ ይችላሉ።

**ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ዩኤስ**
**ዲስትሪክት ፍርድ ቤት**

E. Barrett Prettyman U.S. Courthouse 333 Constitution Avenue NW Washington, DC 20001

202-354-3080

dcd.uscourts.gov

የስራ ሰዓት: ሰኞ እስከ አርብ፣ 9 a.m. እስከ 4 p.m.

የዩኤስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ከፌደራል ሕግ ጋር በተያያዙ የፍትሃብሔር እና የወንጀል ክሶችን ይመለከታል።

## ሰበር ችሎት

**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሰበር ችሎት**
Historic Courthouse 430
E Street NW
Washington, DC 20001

202-879-2700

dccourts.gov/court-of-appeals

የስራ ሰዓት: ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30
a.m. እስከ 5 p.m.

የዲስ ሰበር ችሎት በዲስ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ የታዩ ክሶች የይግባኝ ጥያቄዎችን ይመለከታል።

**የዩኤስ ሰበር ችሎት ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሰርክዩት**
E. Barrett Prettyman U.S. Courthouse 333 Constitution Avenue NW Washington, DC 20001

202-216-7000

cadc.uscourts.gov

የስራ ሰዓት: ሰኞ እስከ አርብ፣ 9 a.m.
እስከ 4 p.m.

የዩኤስ ሰበር ችሎት ለዲሲ ሰርክዩት በዲሲ ዩኤስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ውስጥ የታዩ የይግባኝ ጥያቄዎችን ይመለከታል።

## የክትትል ኤጀንሲዎች

**ኮርት ሰርቪሰስ ኤንድ ኦፌንደር ሱፐርቪዥን ኤጀንሲ (CSOSA)**
የቤት ውስጥ ጥቃት ማስተካካያ ፕሮግራም 910 Rhode Island Avenue NE Washington, DC 20018

202-442-1824

csosa.gov/supervision/branches/domestic_violence.aspx

የስራ ሰዓት: ሰኞ እስከ አርብ፣ 9 a.m. እስከ 5 p.m.

ይሄ የፌደራል ፕሮግራም በፍርድ ቤት የተፈረዱ ሰዓት እላፊዎች እና ርቀት ጠብቅ ትዕዛዞችን ጨምሮ በቤት ውስጥ ጥቃት ወንጀሎች የተፈረደባቸው ግለሰቦች ላይ የክትትል እና የሕክምና አገልግሎት ይሰጣል።

**ኮርት ሰርቪሰስ ኤንድ ኦፌንደር ሱፐርቪዥን ኤጀንሲ (CSOSA)**
የተጠቂ አገልግሎቶች ፕሮግራም
300 Indiana Avenue NW, Suite 2121
Washington, DC 20001

202-585-7377

csosa.gov/supervision/victim_services.aspx

የስራ ሰዓት: ሰኞ እስከ አርብ፣ 9 a.m. እስከ 5 p.m.

CSOSA ተጠቂዎች ተገቢ ህክምና ማግኘታቸውን፣ ግብአቶች ማግኘታቸውን፣ እና ከሁሉም በላይ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ፣ ለተጠቂዎች እጃቹን የሚዘረጋ የተጠቂ አገልግሎቶች ፕሮግራም አለው።

**ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ቅድመ ችሎት አገልግሎቶች ኤጀንሲ**
633 Indiana Avenue NW, Suite 1120
Washington, DC 20004

202-220-5500

psa.gov

የስራ ሰዓት ሁኔታ የሚወሰነው እንደ ክሱ ዓይነት እና ችሎቱ ነው። እባክዎ ለበለጠ መረጃ ከላይ ያለው ቁጥር ላይ ይደውሉ።

ለአካባቢ እና ለፌደራል የክስ መዝገቦች ድጋፍ የሚሰጠው ይሄ የፌደራል ኤጀንሲ፣ ስለ አዲስ የታሰሩ ወንጀለኞች መረጃ ይሰጣል፣ ስለመፈታት ሁኔታ ጥያቄ ያቀርባል፣ እና የችሎት ፍርድ እየተጠባበቁ ለሚፈቱ ወንጀለኞች ቁጥጥር የማድረግ ሃላፊነት አለው።

**ሱፐርየር ኮርት ኦፍ ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፋሚሊ ኮርት ሶሻል ሰርቪስስ ዲቪዥን (FCSSD)**

የፍርድ ቤት ሕንፃ B
510 4th Street NW, Floor 3
Washington, DC 20001

202-508-1900

dccourts.gov/superior-court/ family-social-services

የስራ ሰዓት: ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30 a.m. እስከ 5 p.m.

FCSSD የዲስትሪክቱ የታዳጊ ወጣቶች የአመክሮ ጊዜ ኤጀንሲ ነው፣ እና በዲስትሪክት የወጣት ታዳጊ የፍትህ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ “የፊተኛው-መጨረሻ” ታዳጊ ወጣቶችን የማገልገል እና መከታተል ሃላፊነት አለው። ከሌሎች ተግባሮች መካከል፣ FCSSD እያንዳንዱን የታሰረውን ወጣት ያጣራል ይገመግማል፣ በሁሉም የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ላይ ለፍርድ ቤቱ ምክር ይሰጣል፣ እና ለሁሉም ፍርድ ቤት ውስት ለተገኙ ወጣቶችን የማዋሃድ እና የመቆጣጠር አገልግሎቶችን ይሰጣል።

## ሌሎች የመንግስት ኤጀንሲዎች እና ግብአቶችን ይምረጡ

**የወንጀል ተጠቂዎች የካሣ አከፋፈል ፕሮግራም**
የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍርድ ቤት
ሕንፃ A
515 5th Street NW, Room 109
Washington, DC 20001

202-879-4216

dccourts.gov/services/
crime-victims-compensation-matters

የስራ ሰዓት: ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30
a.m. እስከ 5 p.m.

ይሄ ፕሮግራም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ለከፋ ወንጀል ተጠቂዎች ለካሳ ብቁ ሆኑ ሰዎች የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል፣ እንደ የግል መድህን፣ ሚዲኬይድ፣ ሜዲኬር፣ ሶሻል ሴኩሪቲ፣ የቀጣሪ ደሞዝ ቅጠላ ፕሮግራም፣ የሠራተኞች የካሳ ጥቅማጥቅሞች፣ ወይም የሌላ ምንጮች በመሳሰሉ ሌሎች የገንቢ ምንጮች ያልተሸፈኑ ከወንጀል ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ይሸፍንላቸዋል።

**የቤት ውስጥ ጥቃት መመዝገቢያ ማዕከሎች**

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት
H. Carl Moultrie Courthouse
500 Indiana Avenue NW, Room 4550
Washington, DC 20001

202-879-0152

dccourts.gov/superior-court

የስራ ሰዓት: ሰኞ፣ 8 a.m.
እስከ 4 p.m.
ማክሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30 a.m. እስከ 4 p.m.

በዲስ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመመዝገቢያ ማዕከል የጊዜያዊ ጥበቃ ትዕዛዝ (TPO) ጥያቄዎችን ጨምሮ ሁሉንም ጥያቄዎች ያስተናግዳል። TPO በሞልትሪ ፍርድቤቶች ውስጥ የሚካሄዱት ችሎቶች ከዳኛ በፊት በግል ይከናወናሉ። ይሄ ማዕከል የማማከር አገልግሎት፣ የማህበረሰባዊ አገልግሎት፣ እና ለደንበኞች የሕግ ድጋፍ ይሰጣል።

ዩናይትድ ሜዲካል ማዕከል (D.C. SAFE) ግሬተር ሶውዝኢስት መመዝገቢያ ማዕከል 1328 Southern
Avenue SE, Room 311
Washington, DC 20032

202-561-3000

dcsafe.org

የስራ ሰዓት: ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30
a.m. እስከ 4 p.m.

ዘ ግሬተር ሶውዚስት መመዝገቢያ ማዕከል የመጀመሪያዎቹን የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ (CPO) እና ብያኔዎች ክስ መመስረቶችን ያስተናግዳል። በዚህ ማዕከል ውስጥ ደንበኞች TPO መጠየቅ ይችላሉ፣ እና ችሎቶች የሚከናወኑት በቴሌኮንፈረንስ ነው። CPO ለማግኘት፣ ወደ ዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሞልትሪ ፍርድ ቤቶች ውስጥ መሄድ አለባቸው። ይሄ ማዕከል የማማከር አገልግሎት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት እና ለተጠቂዎች የሕግ ድጋፍ ይሰጣል።

ሁለቱም መመዝገቢያ ማዕከላት ከፍርድ ቤት፣ D.C. SAFE፣ MPD፣ OAG፣ እና USAO-DC እንደዚሁም ከቤት ውስጥ ጥቃት ተጠቂዎች እና የተረፉ ሰዎችን የሚያገለግሉ ድርጅቶች ላይ ተወካዮች አሏቸው። ለበለጠ መረጃ dccourts.gov/superior-court/domestic-violence-unit ይጎብኙ።

**ኦፊስ ኦፍ ዘ ቺፍ ሜዲካል ኤግዛማይነር (OCME)**
401 E Street SW Washington,
DC 20024

202-698-9000
202-442-8797 | TTY

ocme@dc.gov ocme.dc.gov

የስራ ሰዓት: ሰኞ እስከ አርብ፣ 8 a.m.
እስከ 4:30 p.m.

OCME የሚከተሉትን አገልግሎቶች ያቀርባል: የአክሬን ማቃጠል፣ የሰውነት አካል ልገሳ እና በባህር ላይ የቀብር ስነ ስርዓት፣ የሞት ምርመራ፣ የውሂብ ውህደት እና ኢፒዲሞሎጂ፣ የግድያ ግምገማ አገልግሎቶችን፣ የአባዲና ቶኪስኮሎጂ
ላብራቶሪ አገልግሎቶች፣ የሐዘን ማማከር አገልግሎት፣ እና ዕቃዎችን በሐራጅ የመሸጥ አገልግሎት ይሰጣል።

**የዲሲ ማረሚያ ቤቶች VINELink**
ቪክቲም ኢንፎርሜሽን ኖቲፊኬሽን ኤቨሪዴይ (VINE) ሰርዓት

1-877-329-7894 | 24 ሰዓት
1-866-847-1298 | TTY

vinelink.com

የዲሲ የማረሚያ ቤቶች መምሪያ እንደ የእርስዎ ደህንነት ዕቅድ አካል VINELink ያቀርባል። VINELink ስለ ወንጀል ፈፃሚው is an online resource that allowsየአሁኑ የእስር ሁኔታ፣ መለቀቅን፣ መዘዋወርን፣ ወይም ማምለጥን ጨምሮ መረጃ መፈለግ እና በራስሰር ስልክ እና ኢሜይል ማሳወቅ የሚፈቅድ የመስመር ላይ ግብአት ነው። ለጥበቃ ሙሉ ለሙሉ VINE ላይ አይሞርከዙ። አደጋ ውስጥ ነኝ ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ ወንጀለኛው አስቀድሞ እንደተለቀቀ አይነት አስበው ተገብቢውን ቅድመ ጥንቃቄ ያድርጉ።

## ለጅማሪ ያህል

አብዛኛዎቹ የመንግስት ኤጀንሲዎች እና መስሪያ ቤቶች ከዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ያቀርባሉ። እነዛ ለማግኘት፣ የመጀመሪያው ምርጡ ቦታ እዚህ መመሪያ ሲጠቀስ የነበረው የዲሲ ተጠቂዎች የነፃ ስልክ መስመር ነው።

የዲሲ ተጠቂዎች ነፃ የስልክ መስመር ነፃ፣ ሚስጥራዊ መረጃ እና የድጋፍ አገልግሎቶችን ከሚያቀርቡ ተከራካሪዎች ጋር ተጠቂዎችን የሚያገናኝ የ24 ሰዓት፣ የፖሊስ ያልሆነ አገልግሎት ነው። ነፃ የስልክ መስመሩ እንደ የድንገተኛ መጠለያ፣ የድንገተኛ ጊዜ የጤና አገልግሎት፣ የሐዘን ማማከር አገልግሎት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት ግብአቶች፣ እና የሕግ ድጋፍ የመሳሰሉ ግብአቶችን ለተጠቂዎች ይሰጣል።

የዲሲ ነፃ የስልክ መስመርን በዚህ ቁጥር ይደውሉ

## 1-844-4-HELPDC (1-844-443-5732)

ለበለጠ መረጃ dcvictim.org ን ይጎብኙ። ለድንገተኛ

ድጋፍ፣ 911 ላይ ይደውሉ።




## ዲ.ሲ የወንጀል ፍትህ አሰጣጥ ስርዓት ካርታ

ይሄ ከገጽ 6 ላይ የተካተተው የወንጀል ፍትህ አሰጣጥ ርዓት ካርታ ይልቅ በጣም በዝርዝር ይዘት የቀረበ ነው።


ተከሳሹ እንደታሰረ ይቆያል
ተከሳሹ ፍርድ እስከሚሰጥ ድረስ ይለቀቃል
ተከሳሽ የእምነት ቃል ይሰጣል
የአቋም ችሎት
የክስ መዝገቡ ይዘጋል
ችሎት
የፍርድ ብይን መስጠት
ወንጀለኛ ተብሎ
የፈራዶዎች አለመስማማት
ወንጀለኛ አይደለም ፍርድ (ተከሳሽ ይለቀቃል)
የአመክሮ ጊዜ
እስራት፣ አመክሮ ጊዜ ይከተላል
እስራት፣ ከዛም በክትትል ስር መለቀቅ
የእምነት ቃል መስጠት
በድጋሚ ለፍርድ ማቅረብ ሁኔታ
የክስ መዝገቡ ይዘጋል
የይግባኝ ሂደት
ጸንቷል (የወንጀለኛነት ፍርድ ጸንቷል)
እስር ቤት በቀጠሮ ቆይ ( ክሱ ተጨማሪ እርምጃ እንዲወሰድበት ወደ መደበኛ ችሎት ይላካል)
ተቀልብሷል (የወንጀለኛነት ፍርድ ተነስቷል፣ አዲስ ችሎት የለም)

# የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች

የመንግስት ሠራተኞች፣ አቃቤ ሕጎች፣ የወንጀለኛው ጠበቆች፣ እና ዳኞችንም ጨምሮ መከበር ያለባቸው በአካባቢ እና በፌደራል ሕጎች የወጡ የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች አሉ። ተጠቂዎች መብታቸው በመንግስት ሠራተኛ ተጥሷል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ ጉዳያቸውን ለተከራካሪዎቻቸው ማሳወቅ አለባቸው። እንደዚሁም ተጠቂዎች ጥሰቱን በተመለከተ ለሚመለከተው የመንግሰት አካል ያላቸውን ቅሬታ ማሳወቅ ይቻላሉ። እንዴት ቅሬት ማቅረብ እንዳለብዎ የበለጠ ለማወቅ፣ ገጽ 57 እና 58 ላይ ይመልከቱ።

## የዲሲ ወንጀል ተጠቂዎች ሕገ መንግስታዊ መብቶች

የዲሲ የወንጀል ተጠቂዎች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፣ እና የዲሲ ሠራተኞች እነዚህ መብቶች በሚገባ ለተጠቂዎች ሳይሸራረፉ እንዲተገበሩ በተቻለቸው መጠን ሕጉን እንዲፈጽሙ ይጠበቃል። ክፍል 23-1901 ላይ የሚገኘው የዲሲ ኮድ የወንጀል ተጠቂ የሚከተሉት መብቶች አለው:

1. ለተጠቂው ክብር እና ግላዊነት መጠበቅ ሲባል በእኩልነት እና በአክብሮት መስተናገድ አለበት።
2. ከተከሰሰው ወንጀለኛ በሚገባ መጠበቅ አለበት።
3. ስለ ፍርድ ሂደት መረጃ እንዲሰጠው ያስፈልጋል።
4. ተጠቂው የሚሰጠውን የማስክርነት ቃል ከሰማ በተጠቂው የሚሰጠው የምስክርነት ቃል ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያመጣል ብሎ ፍርድ ቤት ካመነ ወይም ፍትህ አሰጣጥ ሁኔታው የሚያስገድድ ካልሆነ በስተቀር ፍርድ ብያኔ ሲሰጥ፣ እና የመፍታት፣ የአመክሮ ጊዜ፣ የክስ መዝገብ ሲዘጋ፣ እና የወንጀለኝነት ፍርድ ብይን ከተሰጠ በኋላ ያሉ ድህረ ችሎቶችን ጨምሮ፣ ከጥቃቱ ጋር በተያያዘ ከማንኛውም የፍርድ ቤት ሂደት ላይ ማግኘት ይችላል።
5. በክስ መዝገቡ ላይ ለሚቀርቡት ክሶች ከጠበቃው ጋር የመስማማት (ምንም እንኳን ተጠቂው የክስ መዝገቡን ሁኔታ መምራት ባይችልም)።
6. የተጠቂውን ኪሳራ ወይም ጉዳት እንዲከሰት ያደረገው ወንጀለኛ ከሆነው ሰው የካሳ ክፍያ እንዲቀበል ትዕዛዝ የማግኘት መብት።
7. ስለ ውንጀላ፣ የፍርድ ብያኔ መስጠት፣ እስራት፣ ከማቆያ መግባት፣ እና ወንጀለኛን መልቀቅ፣ እና የአጥቂውን የወንጀል መዝገቦች ለመዝጋት የተፈረደ ፍርድ የማየት ትዕዛዝ መረጃዎችን ማግኘት መቻል።
8. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ኣና በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ህጎች ውስጥ ያሉ መብቶች ማስታወሻ ማግኘት።
9. የደህንነት ዕቅድ እና ተገቢ አገልግሎቶችን ለማገንባት ስለማንኛውም የሚገኝ የተጠቂ ተከራካሪ እና ማንኛውም ተገቢ ግለሰብ በተመለከተ መረጃ ማግኘት።

## በታዳጊ ወጣት የፍትህ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ የዲሲ ተጠቂዎች መብት

በወንጀል የተከሰሰው ሰው በዲሲ የታዳጊ ወጣቶች የፍትህ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ እየተከሰሰ ያለ ታዳጊ ወጣት ከሆነ፣ ተጠቂው የሚከተሉት መብቶች አሉት፡

1. በአክብሮት፣ በክብር፣ በታዛዥነት፣ ስሜት በሚጠብቅ መልኩ፣ እና ግላዊነታቸውን በሚጠብቅ ሁኔታ መታየት።
2. ስለ ሁሉም ችሎቶች እና ክሶች ስለቀኑ እና ስለጊዜው ማስታወቂያ እንዲደርሰው ማድረግ ነው።
3. በተቻለ መጠን ከምላሽ ሰጪው ተከሳሾች፣ ጓደኞቸው እና ቤተሰቦቻቸው የተለየ መጠባበቂያ ቦታ እንዲሰጠው ያስፈልጋል።
4. ለማንኛውም የገንዘብ የገንዘብ ድጋፍ፣ ካሣ፣ እና ሌሎች የሚገኙ የማህበረሰባዊ አገልግሎቶች መረጃ ማግኘት።
5. ለማስረጃ ካልተያዘ በስተቀር የተሰረቁ እና ሌሎች ንብረቶች በፍጥነት እንደመለሱት።
6. የሚቻል ከሆነ፣ ተጠቂው የካሣ ጥያቄ መጠየቅ ኣንደሚችል በኦፊስ ኦፍ ዘ አተርኒ ጀነራል ፎር ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሊነገረው ይገባል።
7. የተጠቂ ጉዳት ሀተታ የማስገባት፣ እና ክሱ በሚመሰረትበት ጊዜ ይሄ ሀተታ ከግምት ውስጥ እንዲገባለት የመጠየቅ መብት።
8. በተከሳሹ ወንጀለኛ፣ በቤተሰቦቹ፣ ምስክሮቹ እና በተጠቂው መካከል ያለውን የመገናኘት አዝማሚያ ለመቀነስ ተገቢው ጥበቃ እንዲደረግለት ያስፈልጋል።

በተጨማሪም፥

- በሕግ ካልተደነገገ በስተቀር፣ ከችሎቱ በፊት የተጠቂውን ስም ወይም አድራሻ የዲሲ መንግስት ማውጣት አይኖርበትም።
- የወንጀል ተከሳሹ፣ ጠበቃው፣ ወይም እሱን ወክሎ የሚገኘው ማንኛውም ግለሰብ ከተጠቂው፣ ከተጠቂው ቤተሰብ፣ ወይም ከምስክሩ ጋር በሚገናኙበት የመጀመሪያ ጊዜ ተከሳሹን፣ ለእሱ ጥብቅና እንደቆሙ፣ እሱን ወክለው እንደመጡ በግልጽ ማስረዳት አለባቸው።

*ይሄ የክፍል 16-2340 የሆነው የዲሲ ኮድ ማጠቃለያ ነው። ሙሉውን የሕግ ጽሁፍ ለማየት ደንቡን ይመልከቱ።*

## የፌደራል የወንጀል ተጠቂዎች መብት አዋጅ

የፌደራል ወንጀሎች ተጠቂዎች በፌደራል የወንጀል ተጠቂዎች መብት ድንጋጌ (18 U.S.C. § 3771) መሰረት የሚከተሉት መብቶች አላቸው:

1. ከተወነጀለው ግለሰብ ድህንነታቸው የመጠበቅ መብት።
2. ስለ ማንኛውም የክፍት ችሎት ሂደት፣ ወይም ወንጀሉን በሚመለከት ወይም የታሰረው ግለሰብ ማምለጥ ጨምሮ ማንኛውም የአመክሮ ጊዜ ችሎት ላይ፣ ምክንያታዊ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ የማግኘት መብት።
3. ፍርድ ቤቱ ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ ካገኘ በኋላ ተጠቂው በችሎት ላይ የሌላ ሰው ምስክርነት ከሰማ የተጠቂው ምስክርነት ላይ የከፋ አስተዋጾ ይኖረዋል ብሎ ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ በስተቀር፣ ከማንኛውም ክፍት ችሎት የሚሰማበት ሂደት ላይ ያለመነጠል መብት።
4. መፈታትን፣ የእምነት የክህደት ቃል መስጠትን፣ ወይም ማንኛውም የአመክሮ ጊዜ ችሎት ጨምሮ  በዲስትሪክት ፍርድ ቤት ውስጥ ማንኛውም ክፍት ችሎት ላይ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የመሰማት መብት።
5. በክስ መዝገቡ ላይ ከመንግስት ጠበቃ ከሆነው ግለሰብ ጋር የመስማማት መብት።
6. በሕጉ እንደተደነገገው ሙሉለሙሉ እና በቶሎ የካሣ ክፍያ የማግኘት መብት።
7. ምክንያታዊ ያልሆነ የፍርድ መዘግየት ጊዜ የመክሰስ መብት።
8. ለተጠቂዎቹ ክብር እና ግላዊነት ሲባል በእኩልነት እና በአክብሮት የመታየት መብት።
9. ማንኛውንም የእምነት የክህደት ቃል ድርድር ወይም የተለየ ለፍርድ የማቅረብ ስምምነት ላይ ወዲያውኑ በጊዜው የማወቅ መብት።
10. በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን መብቶች የማወቅ የመነገር እና በክፍል 503(c) የተጠቂዎች መብቶች እና ካሣ አዋጅ (42 U.S.C. § 10607(c)) ላይ የተገለጹትን መብቶች የማወቅ እና ለኦፊስ ኦፍ ዘ ቪክቲምስ ራይትስ ኦምቡስማን ዲፓርትመንት ኦፍ ጀስትስ የማግኛ አድራሻ የማግኘት መብት ነው።

## የወሲብ ትንኮሳ አገጋሚዎች ቢል ኦፍ ራይትስ

ከወሲብ ጥቃት የተረፉ ሰዎች በፌደራል ሕግ የተደነገጉ የሚከተሉት መብቶች አሏቸው:

1. የሕክምና አባዲና ምርመራን ያለመከልከል፣ ወይም ክፍያ አለመጠየቅ፣ የማግኘት መብት።
2. በሕገ ደንብ ላይ በሰፈረው የመጨረሻው የጊዜ ወሰን ድረስ፣ ወይም ለ20 ዓመታት፣ ከዛም ያነሰ ጊዜ፣ የወሲብ ጥቃት ማስረጃ ስብስብ መሳሪያ እና በውስጡ ያሉ ማስረጃዎችን ያልምንም ክፍያ በጥንቃቄ እንዲቀመጡ የማድረግ መብት።
3. የዲኤንኤ አቻ ውጤት፣ የቶክሲሎጂ ሪፖርት፣ ወይም ማንኛውም የሕክምና አባዲና ምርምራ ውጤት ጋር በተያያዘ የተሰበሰበ ሌላ መረጃ ጨምሮ በሂደት ላይ ያለን ምርመራ የማያስተጓጉል ወይም የማያበላሽ ከሆነ ስለውጤቱ የማወቅ መብት።
4. የወሲብ ጥቃት ማስረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያን በተመለከተ የአሰባሰብ እና የማስቀመጥ ፖሊሲዎችን የሚገልጽ በጽሁፍ የተፃፈ ድብዳቤ የማግኘት መብት።
5. ከታቀደው የመሳሪያ ማቃጠያ ወይም የማስወገጃ ቀን ከ60 ቀናት በፊት ያላነሰ ጊዜ ውስጥ የማስረጃ ስብስብ መሳሪያውን እየጠበቀ ካለው ተገቢው መኮንን፣ በጽሁፍ በደብዳቤ ከተጠየቀ በኋላ፣ የተፃፈ የማሳወቂያ ደብዳቤ የማግኘት መብት።
6. በጽሁፍ ማመልከቻ ከገባ በኋላ፣ መሳሪያውን ወይም በውስጡ ያሉ ጠቃሚ ማስረጃዎችን ለተጨማሪ ጊዜ ሳይወገዱ እንዲቆዩ የማድረግ መብት።
7. እነዚህን መብቶች የማወቅ መብት።

*ይሄ የተረፉ ሰዎች ህገ መንግስታዊ መብት አዋጅ 2016 ማተቃለያ ነው። (የሕዝብ ሕግ ቁጥር 114-236 (10/07/2016)።*

## የሕፃናት ተጠቂዎች መብቶች

ሕፃናት ተጠቂዎች በፌደራል ሕግ የተደነገጉ የሚከተሉት መብቶች አላቸው፥

1. በአንዳንድ ክሶች ላይ፣ ሁለት ቦታ ላይ የሚሰራጭ ዝግ ሰርኪዩት ቴሌቪዥን በመጠቀም፣ ወይም ደግሞ ከችሎቱ በፊት ቃለ መሃላ በሚፈጸምበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ከችሎቱ በፊት ሕፃኑ ቃል እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል።
2. የሕፃን ተጠቂ ማንነት በድብቅ መያዝ አለበት።
3. የሚቻል ከሆነ፣ ፖሊሲን፣ አቃቤ ሕግን፣ ዶክተሮችን፣ እና የቴራፒ ሰዎችን ጨምሮ፣ የሕፃን ጥቃት ቡድን የተጠቃውን ሕፃን ለመደገፍ እና የአዕምሮ ችግርን ለመቀነስ መደራጀት አለባቸው።
4. በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ዳኛው በመዝገቡ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ጉዳይ የሌለው ሰው ላይ ፍርድቤቱ እንዲዘጋ ሊያደርግ ይችላል።
5. በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፣ ለሕፃኑ የተሻለ አማራጭ በፍርድ ቤቱ ሂደት ላይ የሚከራከርለት ልዩ ጠባቂ ሊሾምለት ይችላል።
6. ምስክርነት በሚሰጥበት ጊዜ፣ ሕፃኑ በአዋቂ የሚታጀብበት እና የሚደገፍበት መብት አለው።

*ይሄ በ 18 U.S. ኮድ § 3509 ላይ የተዘረዘሩ መብቶች ማጠቃለያ ነው።*

**ኮሚሽን ኦን ጁዲሻል ዲሳቢሊቲስ ኤንድ ቴነር**
515 5th Street NW, Suite 246
Washington, DC 20001

202-727-1363
202-727-1363 | TTY

dc.cjdt@dc.gov
cjdt.dc.gov

የስራ ሰዓት: ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30 a.m. እስከ 5 p.m.

ይሄ ኮሚዚዮን የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሰበር ችሎት እና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች የተፈጸሙ አግባብ ያልሆኑ ባህሪያትን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይገመግማል። ኮሚስዩኑ የሚከተለውን አይገመግምም
ውሳኔ በሚሰጥበት የፍርድ መዝገብ ላይ በእነዚህ ዳኞዎች የተሰጡ ውሳኔዎች ቅሬታ በአንድ የክስ መዝገብ ውስጥ ስለተሰጠ የዳኛ ውሳኔ በተመለከተ ቅሬታ ለማድረግ ኮሚስዩኑን አይጠይቁ። አቃቤ ሕግ በአንድ በተለየ የክስ መዝገብ ላይ የአንድን ዳኛ ውሳኔ መገምገም በመፈለግ ሂደት ላይ ማብራሪያ መስጠት ይችላል።

**ዲሲ ኦፊስ ኦፍ ፖሊስ ኮምፕሊያንትስ (OPC)**
1400 I Street NW, Suite 700
Washington, DC 20005

202-727-3838
1-866-588-0569 | 24-ሰዓት ነፃ የስልክ መስመር
711 | TTY

policecomplaints.dc.gov

የስራ ሰዓት: ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30 a.m. እስከ 5 p.m.

OPC ከሜትሮፖሊቲያን ፖሊስ ዲፓርትመንት (MPD) እና ዲሲ ሃውሲንግ አውቶሪቲ ፖሊስ ዲፓርትመንት (DCHAPD) ውጪ ያለ እራሱን የቻለ ተቋም ነው።
በሲቪል ሠራተኞች የተሞላው OPC ስድስት ዓይነት በፖሊስ መኮንን ላይ የቀረቡ የዜጎች ቅሬታዎችን ይመረምራል: አግባብ ያልሆነ የዘር የፆታ ተጠቂ መሆን
ቋንቋ አጠቃቀም ወይም ጸባይ፣ የመልስ ምት፣ ያልተፈለገ እና ከመጠን በላይ የሆነ ሃይል መጠቀም፣ የዘር መድሎ
ለመለየት አለመቻል። OPC እንደዚሁም በኤምፒዲ የድረገጽ (ከታች ይመልከቱ) ላይ የሚገኘውን የምስጋና ቅጽ በማስገባት ዜጎች ጥሩ አርዓያ መሆን የሚችሉ የፖሊስ መኮንኖችን ማመስገን እንደሚችሉ ዕድሉን ይሰጣል።

**ጁዲሻል ካውንስል ኦፍ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ**
ማስታወቂያ: ሰርኪዩት ኤክስኪዩቲቭ
E. Barrett Prettyman U.S. Courthouse
333 Constitution Avenue NW
Washington, DC 20001

202-216-7340

cadc.uscourts.gov/internet/home.nsf/content/Judicial+Misconduct

የጁዲሻል ካውንስሉ በዩኤስ ኮርት ኦፍ አፒልስ ፎር ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሰርክዩት እና ዘ ዩኤስ ዲስትሪክት ኮርት ፎር ዘ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ያሉ ዳኞች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይገመግማል፣ ነገር ግን እነዚህ ዳኞች ውሳኔ ላይ ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች አይደለም። በክስ መዝገብ ውስጥ ዳኛው ስለወሰነው ውሳኔ ቅሬታ ለማቅረብ የጁዲሻል ካውንስሉን አያግኙ። አቃቤ ሕግ በአንድ በተለየ የክስ መዝገብ ላይ የአንድን ዳኛ ውሳኔ መገምገም በመፈለግ ሂደት ላይ ማብራሪያ መስጠት ይችላል።

**ሜትሮፖሊቲያን ፖሊስ ዲፓርትመንት ኢንተርናል አፊይርስ ዲቪዥን** (IAD)
64 New York Avenue NE Washington, DC 20002

202-727-4385
1-800-298-4006 | 24-ሰዓት ነፃ የስልክ ጥሪ
202-898-1454 | TTY
citizen.complaints@dc.gov
mpdc.dc.gov/page/ internal-affairs-bureau
mpdc.dc.gov/page/how-file-citizen-complaint-or-commendation

IAD የኤምፒዲ ውስጣዊ ክፍል ሲሆን ሃላፊነቱም የፖሊስ መኮንኖች ላይ የሚነሱ ሁሉም የብልሹ ባህሪዎች ቅሬታዎች በትክክል እየተስተናገዱ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። IAD በዲስ የፓሊስ ቅሬታ እና ስማቸው የማይጠቀስ ቅሬታዎች በኩል የሚመረመሩትን ብልሹ ባህሪያቶችን ጨምሮ ማንኛውም ዓይነት ብልሹ ባህሪ በግልጽ በማሳወቅ የተከፈቱትን የክስ ፋይሎች ላይ ምርመራዎችን ያደርጋል። እንደዚሁም ዜጎች በኤምፒዲ የድረገጽ ላይ በመሄድ የምስጋና ቅጽ በማስገባት ማህበረሰቡን ማገልገል ላይ ጥሩ አርዓያ ሥራ የሰሩ የፖሊስ መኮንኖችን ምስጋና ማቅረብ ይችላሉ።

**ዩኤስ ዲፓርትመንት ኦፍ ጀስትስ ኦፊስ ኦፍ ቪክቲምስ ራይት ኦምብስማን**
Executive Office for U.S. Attorneys 950 Pennsylvania Avenue NW,
Room 2261
Washington, DC 20530

202-252-1010
1-877-574-9302 | ከፍያ ነፃ ጥሪ
usaeo.VictimOmbudsman@usdoj.gov
justice.gov/usao/resources/crime-victims-rights-ombudsman

የስራ ሰዓት: ሰኞ እስከ አርብ፣ 9 a.m. እስከ 5 p.m.

ይሄ የፌደራል ቢሮ በወንጀል ተጠቂዎች መብት አዋጅ 2004 ስር የተጠቂዎች የፌደራል መብቶች በበፍትህ አሰጣጥ መምሪያ ሠራተኞች ስለመጣሱ በግልጽ በፌደራል ወንጀል ተጠቂዎች የቅሬታ ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ያዳምጣል።

በዲሲ የፍትህ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ ስለሚሰሩ ባለሙያዎች እንዴት ቅሬታ ማንሳት ወይም ማቅረብ እንደሚቻል ለማወቅ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ እዚህ ላይ ይጎብኙ courtexcellence.org/uploads/publications/Compliments_Complaints_Guide_2013.pdf.

## የቃላት መፍቻ

**የተወነጀለ (Accused)**
ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የሚጠረጠር ግለሰብ ሆኖም ግን በፍርድ ቤት ያልተረጋገጠበት ግለሰብ። (እንደዚሁም *ተከሳሽ* ( *Defendant* ) እና *ወንጀለኛ (Offender)* ይመልከቱ)

**ከወንጀል ነጻ መሆን (Acquittal)**
ተከሳሹ ወንጀሉን እንዳልፈጸመ በማስረጃ ሊረጋገጥ ስላልቻለ ዳኛው ወይም ፈራዶዎቹ የሚወስኑት ውሳኔ።

**ይግባኝ ማለት (Appeal)**
ክሱ በድጋሚ እንዲታይ ለበላይ ፍርድ ቤት ኤቤቱታ ማስገባት። የበላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ሊያጸና (ሊያጸድቅ)፣ ሊቀለብስ (ሊሽር እና ውድቅ ሊያደርግ)፣ እንዲታረም (በህግ ስህተት የተነሳ ወደታችኛው ፍርድ ቤት ተመልሶ ክሱ እንዲታይ ማዘዝ) ሊያደርግ ይችላል።

**አሬንመንት (Arraignment)**
በአንድ ወንጀል የተከሰሰ ግለሰብ ከዳኛ ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ቀርቦ በእሱ ላይ የተነሱት ክሶች ተደምጠው ወንጀሉን መፈጸሙን የእምነት የክህደት ቃሉን የሚሰጥበት የመጀመሪያው ችሎት። (እንደዚሁም *ፕሬዘንትመንትን* ይመልከቱ)

**እስራት (Arrest)**
አንድ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ለተወነጀለ ግለሰብ ክስ እንዲመሰረትበት እና ወንጀሉን ስለፈጸሙ በፍርድ ቤት ችሎት እንዲፈረድበት ወደ ጊዜያዊ ማቆያ ቦታ መውሰድ።

**ክስ (Charge)**
ተከሳሹ ጥሶታል ተብሎ በአቃቤ ህግ ለፍርድ የሚቀርብበት ልዩ ህገ ደንብ።

**የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ (CPO)**
በሁለት ሰዎች መሀል መገናኘትን የሚከለክል፥ በቤት ውስጥ ጥቃት ጊዜ ጊዜያዊ አሳዳጊነት እና የመኑብኛ መርሀ ግብሮችን የሚያስቀምጥ፥ በቤት ውስጥ ጥቃት ችግሮች የተነሳ ለመጠጥ እና አደንዛዥ ዕጽ ሱስ፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ወይም የወላጅ አስተዳደግ ክህሎት ላይ የሕክምና ፕሮግራሞችን የሚነድፍ፥ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ነው። ምላሽ ሰጪው (በትዕዛዙ ባህሪው የሚገደበው ግለሰብ) ለ CPO ችሎት ጊዜ ፍርድ ቤት የመገኘት መብት አለው።

**ክሪሚናል ጀስትስ አክት (CJA) አተርኒ**
ጠበቃ ካልተቀጠረለት በስተቀር ጠበቃ ለመቅጠር የማይችል ተከሳሽ በጥብቅና የሚቆም በፍርድ ቤቱ የሚሾም እና የሚቀጠር ጠበቃ ነው። (እንደዚሁም *የሕዝብ ተከራካሪ* ይመልከቱ)

**ኮንቲኑአንስ (Continuance)**
የፍርድ ቤት ችሎት ቀን ቀጠሮ ወደ ሌላ ቀን ወይም ሰዓት ማስተላለፍ።

**ኮንቪክሽን (Conviction)**
አንድ ተከሳሽ ለተከሰሰበት ክስ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥበት ወንጀለኛ ተብሎ በዳኛው ወይም በፈራዶዎቹ ውሳኔ ሲሰጥ።

**ፍርድ ቤት (Court)**
ለቀረቡለት የሕግ ጥያቄዎች እና አለመግባባቶችን ላይ ውሳኔ የሚሰጥ የሕግ ስልጣን ያለው የመንግስት የፍትህ ሰጪ ቅርንጫፍ ኤጀንሲ ነው።

**ተከሳሽ (Defendant)**
ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ክስ የተመሰረተበት ግለሰብ። (እንደዚሁም *የተወነጀለ (Accused)* እና *ወንጀለኛ (Offender)* ይመልከቱ)

**የተከሳሽ ጠበቃ (Defense Attorney)**
ለተካሳሹ ጥብቅና የሚቆመው ጠበቃ።

**የቤት ውስጥ ጥቃት (Domestic Violence)**
አንድ ሰው በፍቅር ግንኙነት ወይም በቤተሰብ ግንኙነት ጊዜ እንደ መማታት፣ ማስፈራራት፣ ንብረቶችን ማውደም፣ ወይም ሌሎችን ለመቆጣጠር የስሜት ጥቃት የመሳሰሉ የተለያዩ ዓይነት የጥቃት ባህሪ የሚያሳይበት በስርዓት የተቀረጸ የባህሪ ንድፍ ነው።

**ማስረጃ (Evidence)**
በአቃቤ ሕጉ እና በተከሳሹ ጠበቃ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ የምስክርነት ቃል፣ መረጃ ወይም ኤክዚቢት።

**ከባድ ወንጀል (Felony)**
በአብዛኛው ከአንድ ዓመት በላይ በእስር ቤት የሚያቆይ እና የገንዘብ ቅጣት የሚታስቀጣ ከባድ ወንጀል ነው። ከባድ ወንጀሎች እንደ ግድያ፣ አስገድዶ መድፈር፣ በር ሰብሮ ዝርፊያ እና ስርቆትን ያካትታል።

**የበላይ ፈራዶ (Grand Jury)**
በአቃቤ ሕጉ የሚቀርቡትን ማስረጃዎች የሚያደምጡ እና ተጠርጣሪውን ላይ ክስ ለመመስረት እና በችሎት ለማቅረብ በቂ ማስረጃ እንደቀረበ ወይም እንዳልቀረበ የሚወስኑ 23 የዲሲ ነዋሪዎች ቡድን።

**ወንጀለኛ ተብሎ ሲፈረድ (Guilty)**
አንድ ወንጀለኛ በወንጀል ክስ በተከሰሰበት ክስ ወንጀሉን መፈጸሙ በዳኛ ወይም በፈራዶ ሲወሰን።

**የእምነት ቃል መስጠት (Guilty Plea)**
አንድ ተከሳሽ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ በችሎት ውስጥ ቀርቦ በራሱ ላይ ሲመሰክር።

**የክስ ማስረጃ ኢንዳይትመንት (Indictment)**
ተጠርጣሪው ወንጀል ስለመፈጸሙ የሚያብራራ በበላይ ፈራዶዎች የሚረቅ የክስ ማስረጃ ጽሁፍ።

**ምርመራ (Investigation)**
ፖሊስ እና ወይም አቃቤ ሕጎች በቂ ማስረጃ እስከሚያገኙ እና አንድን ግለሰብ ለወንጀሉ ለፍርድ እስከሚያቀርቡ ድረስ የሚቀጥል ወንጀሉ እንደተፈጸም እና እንዳልተፈጸመ ማረጋገጥ እና ማን እንደፈጸመው ለማወቅ በፖሊስ እና በአቃቤ ሕግ የሚደረግ የመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ነው።

**ዳኛ (Judge)**
በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ፣ በፍርድ ቤት ውስጥ ህግን ለማስፈጸም ሲባል በዲሲ ጁዲሻል የጥቆም ኮሚሽን
ከታጨ በኋላ ለዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝደንት የሚጠቆም፣ እና በፕሬዝደንቱ ከተሾመ በኋላ በሴኔት የሚጸድቅ ግለሰብ ነው።

**ፈራዶ (Jury)**
በፍርድ ቤት ውስጥ የሚቀርብን ማስረጃ የሚያዳምጡ እና ተከሳሹ ወንጀለኛ እንደሆነ በበቂ አሳማኝ ማስረጃ መንግስት እንዳስመሰከረ እና እንዳላስመሰከረ የሚወሰኑ የዲሲ ነዋሪዎች ቡድን ናቸው።

**ዝቅተኛው ብያኔ (Mandatory Minimum)**
ይሄ በህግ የተፃፈ የፍርድ ብይን ነው። ዝቅተኛ ብያኔ የተቀመጠለትን ወንጀል አንድ ወንጀለኛ በሚፈጽምበት ጊዜ፣ ዳኛው በሕግ የተፃፈውን ብያኔ መጠቀም አለበት።

### ቀላል ወንጀል (Misdemeanor)
ከከባድ ወንጀል ያነሰ ወንጀል ሲሆን በአብዛኛው ከአንድ ዓመት ባልበለጠ የእስራት ጊዜ እና/ወይም የገንዘብ ቅጣት የሚያስፈርድ ወንጀል ነው።
ቀላል ወንጀሎች እንደ ጥቃቅን ስርቆት፣ አብዛኛዎቹ የትራፊክ ሕግ ጥሰቶች፣ እና አሺሽ ይዞ መገኘት የመሳሰሉ ጥቃቶች ናቸው።

### ያለምንም ክርክር ፍርድ መቀበል (No Contest Plea)
ተከሳሹ ክሱን እንዳልፈጸመ የክህደት ቃሉን ሰጥቶ ሆኖም ግን ቅጣቱን ለመቀበል ኣንደተስማማ የሚገልጽ የጽሁፍ ማመልከቻ ነው።

### የክህደት ቃል መስጠት (Not Guilty Plea)
ተከሳሹ ወንጀሉን እንዳልፈጸመ የክህደት ቃሉን የሚሰጥበት ሁኔታ።

### ወንጀለኛ (Offender)
ወንጀል እንደፈጸመ የተረጋገጠበት ግለሰብ።

### ሰነድ ማሰባሰብ (Papering)
አቃቤ ሕግ በተጠርጣሪው ላይ ክስ ለመመስረት ወይም ላለመመስረት የሚያደርገው ውሳኔ።

### የሐሰት ምስክርነት (Perjury)
አንድ ሰው እውነት ለመናገር ቃለ መሓላ ከፈጸመ በኋል የሚናገርው ውሸት።

### የግል ቃል መስጠት (Personal Recognizance)
ተጠርጣሪው በፍርድ ቤት በሚታዘዝበት ጊዜ ወደ ፍርድ ቤት እንደሚመጡ የሚያሳውቅ በጹሁፍ የተቀመጠ የቃል ማስተማመኛ ነው፣ በዲሲ የወንጀል ክሶች ውስጥ በአብዛኛውም ቅድመ ችሎት የመለቀቂያ መንገድ ነው።

### የእምነት የክህደት ቃል መስጠት (Plea)
ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንደፈጸመ የሚያምንበት ወይም የሚክድበት በፍርድ ቤት ውስጥ ተከሳሹ የሚሰጠው መልስ ነው።

### የእምነት የክህደት ቃል ድርድር (Plea Bargain)
ተከሳሹ ስለወንጀሉ የእምነት ቃሉን እንደሚሰጥ በአቃቤ ሕግ እና በተከሳሹ መካከል የሚደረግ ስምምነት።

### ቅድመ ችሎት (Preliminary Hearing)
በክስ መዝገቡ ላይ ለመቀጠል በቂ መረጃ እንዳለ ለማወቅ የሚደረግ ችሎት።

### ቅድመ ብያኔ ሪፖርት (Pre-sentence Report)
የተከሳሹን ያለፈውን ባህሪ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ እና ስብዕና፣ እንደዚሁም ስለተፈጸመው ወንጀል ድርጊት ዝርዝር ማስረጃ የሚያቀርብ በ ኮርት ሰርቪስስ ኤንድ ኦፌንደር ሱፐርቪዥን ኤጀንሲ (CSOSA) የሚዘጋጅ ሪፖርት ነው። ሪፖርቱ ዳኛው የፍርድ ብያኔ ለመስጠት ያስችለዋል። (እንደዚሁም *የተጠቂ ጉዳት ሁተታን* ይመልከቱ)

### ፕሪዘንትመንት (Presentment)
በዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ፣ በከባድ ወንጀል የተከሰሰ ሰው ከዳኛ
ፊት ቀርቦ፣ ስለተከሰሰበት ክስ የሚነገረው፣ እና የእምነት የክህደት ቃሉን እንዲሰጥ የሚጠየቅበት የመጀመሪያው የፍርድ ቤት ችሎት ነው። (እንደዚሁም አሬንመንትን *(Arraignment)* ይመልከቱ)

### ቅድመ ችሎት እስራት (Pretrial Detention)
አንድ ተከሳሽ በወንጀል ከተከሰሰ በኋላ እና ከችሎት በፊት ጊዜያዊ ማቆያ ቦታ ውስጥ ሲቀመጥ።

### አሳማኝ ምክንያት (Probable Cause)
ወንጀሉ እንደተፈጸመ እና ክሱ መቀጠል እንዳለበት ለማመን በፖሊስ፣ በአቃቤ ህግ እና በዳኛው የሚፈለገው የማስረጃ መጠን።

### አመክሮ (Probation)
በአመክሮ ቁጥጥር፣ ወይም በማህበረሰብ ቁጥጥር መኮንን ስር ወንጀለኛው ነፃ እንዲለቀቅ የሚፈቅድ የፍርድ ቤት ብያኔ ነው።

### ማስረጃ ማቅረብ (Proffer)
መጀመሪያ ላይ የሚቀርብ ወይም የሚታይ በንግግር ወይም በማየት የሚሰጥ የምስክርነት ቃል ወይም ማስረጃ። እንደዚሁም የማስረጃ ማቅረብ (offer of proof) ተብሎ ይታወቃል።

### አቃቤ ሕግ (Prosecutor)
በወንጀል የክስ መዝገብ ጊዜ፣ የዲሲ መንግስትን ወክሎ የሚከራከረው ጠበቃ፣ አቃቤ ሕጉ ረዳት የዩኤስ ጠበቃ ነው፣ ወይም ረዳት የዲሲ ጠበቃ ነው።

### የሕዝብ ተከራካሪ (Public Defender)
ጠበቃ ለመክፈል አቅም የሌላቸውን ተከሳሾች የሚወክሉ በፐብሊክ ዲፌንደር ሰርቪስ ፎር ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ወይም ኦፊስ ኦፍ ዘ ፌደራል ፐብሊክ ዲፈንደር የሚቀጠር ጠበቃ። (እንደዚሁም *የክሪሚናል ጀስትስ አክት አተርኒንም ይመልከቱ*)

### የፍርድ ብያኔ (Sentence)
አንድ ተከሳሽ ወንጀለኛ ሆኖ ሲረጋገጥ ዳኛው የሚሰጠው ቅጣት።

### የአቋም ችሎት (Status Hearings)
ስለ ክስ መዝገቡ አቋም አዳዲስ መረጃዎችን ለማቅረብ እና አቃቤ ሕጉ እና የተከሳሹ ጠበቃ ለዋናው ችሎት ዝግጁ መሆናቸውን የሚታይበት ችሎት።

### መጥሪያ (Subpoena)
በፍርድ ቤት ውስጥ ወይም በበላይ ፈራዶ ፊት ስለ ወንጀሉ የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ በተወሰነ ሰዓት እና ቦታ እንዲገኝ ለአንድ ሰው የሚሰጥ የፍርድ ቤት መጥሪያ ወረቀት።

### ተጠርጣሪ (Suspect)
ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የሚታመን እና በምርመራ ውስጥ ያለ፣ ነገር ግን ክስ ያልተመሰረተበት ወይም ያልታሰረ ግለሰብ።

### ጊዜያዊ የጥበቃ ትዕዛዝ (Temporary Protection Order, TPO)
አንድን ሰው ከአንዳንድ ባህሪያቶች እንዲቆጠብ የሚያዝ የፍርድ ቤ ትዕዛዝ። TPO የሚጸናበት ጊዜ 14 ቀናት ነው፣ ከዛ በኋላ የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ (CPO) ያስፈልግ ወይም አያስፈልግ ለማወቅ ችሎት ይኖራል። TPO ትዕዛዝ ለማውጣት ምላሽ ሰጪው (በትዕዛዙ ባህሪው የሚገደበው ግለሰብ) በፍርድ ቤት ውስጥ መገኘት አያስፈልገውም።

### ምስክርነት (Testimony)
እውነቱን ለመናገር መሀላ በፈጸሙ ሰዎች የሚሰጥ የምስክርነት ቃል።

### ችሎት (Trial)
ተከሳሹ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ ያለምንም ጥርጥር በበቂ ማስረጃ አቃቤ ሕግ እንዳስመሰከረ እና እንዳላስመሰከረ ለመወሰን ለዳኛ ወይም ለፈራዶ ማስረጃ የሚቀርብበት የፍርድ ቤት ሂደት ነው።

### ውሳኔ (Verdict)
ተከሳሹ ወንጀሉን እንደፈጸመ እና እንዳልፈጸመ በችሎቱ መጨረሻ ላይ ዳኛው ወይም ፈራዶዎቹ የሚወስኑት ውሳኔ።

### ተጠቂ (Victim)

በወንጀል የተነሳ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተጎዳ ሰው። ይሄ በእሱ ላይ የወንጀል ሙከራ የተሞከረበት ወይም የተፈጸመበት ሰው፣ እና የተገደለው ግለሰብ ቤተሰብ ጨምሮ (ከሌሎች መካከል) ይካትታል።

### የተጠቂ ጥቃት ሀተታ (Victim Impact Statement)

የፍርድ ብያኔ በሚሰጥበት ጊዜ ዳኛው የሚጠቀምበት፣ በተጠቂው ሕይወት እና በተጠቂው ቤተሰብ ላይ ወንጀሉ ያመጣውን አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ የአዕምሮ፣ እና የገንዘብ ጉዳትን በተመለከተ ተጠቂው የሚያብራራበት ጽሁፍ። (እንደዚሁም *ቅድመ የፍርድ ብያኔ ሪፖርት* ይመልከቱ።

### ምስክር (Witness)

ስለወንጀሉ አንድ ነገር ያየ ወይም የሚያውቅ ሰው። ተጠቂውም አብዛኛውን ጊዜ ምስክር ነው።

### የምስክር ስብሰባ (Witness Conference)

ለችሎት ለመዘጋጀት በተጠቂው፣ በምስክር እና በአቃቤ ሕግ መካከል የሚደረግ ስብሰባ።

# የክስ መመዝገቢያ (Case Diary)

**የተወነጀለው/ተከሳሽ/ወንጀለኛው ሰው ስም(ሞች)**

_______________

**የፖሊስ ሪፖርት ቁጥር**

_______________

**የፍርድ ቤት ክስ መዝገብ ቁጥር** *(ስለ የክስ ዝርዝር ሰነድ መረጃ በየነመረብ ላይ ቀጥሎ ይገኛል: [dccourts.gov/cco](dccourts.gov/cco).)*

_______________

**ክስ(ሶች)**

_______________

_______________

_______________

**የወንጀል ቀን**

_______________

**ፕሬዘንትመንት ቀን/አሬንመንት ቀን**

_______________

**የእስር ችሎት ቀን**

_______________

**ቅድሚ ችሎት ቀን**

_______________

**የአቋም ችሎት ቀን(ኖች)**

_______________

**የበላይ ፈራዶ ቀን**

_______________

**የችሎት ቀን**

_______________

**የብያኔ ቀን**

_______________

**ሌሎች አስፈላጊ ቀኖች**

_______________

**የፖሊስ መኮንን ስም እና የመገኛ መረጃ**

_______________

_______________

**የፓሊስ መርማሪ ስም እና የመገኛ መረጃ**

**የአቃቤ ሕግ ስም እና የመገኛ መረጃ**

**የተከሳሹ ጠበቃ/መርማሪ እና የመገኛ መረጃ**

**የተጠቂው ተከራካሪ ስም እና የመገኛ መረጃ**

**የመድህን መረጃ** *(ኩባንያ፣ የኤጀንት ስም፣ የመገኛ አድራሻ፣ እና የመጠየቂያ ቁጥር)*

**ሌሎች ጠቃሚ የመገኛ መረጃዎች**

## ማስታወሻዎች

ማስታወሻዎች

## ማስታወሻዎች

ማስታወሻዎች

## ማስታወሻዎች

## ማስታወሻዎች

# ከካውንስል ፎር ኮርት ኤክሰለንስ ተጨማሪ
# የማህበረሰብ የትምህርት መመሪያዎች

ከ 1982 ጀምሮ፣ የማህበረሰብ ትምህርት የ CCE ዋና ተልዕኮ ክፍል ነበር። እነዚህን እና ሌሎች ህትመቶችን ለማውረድ በ courtexcellence.org/digital-library ላይ የሚገኘውን ዲጂታል ላይብረሪያችንን ይጎብኙ።

- የግል ግንኙነቶች መመዝገቢያ መጽሐፍ (አባሪነቱ ለ.....) [እንግሊዘኛ እና ስፓኒሽኛ]
- እንዴት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ዳኞቹን እንደሚያገኝ
- ስለ ዲሲ የታዳጊ ወጣቶች የፍትህ አሰጣጥ ስርዓት መመሪያ [ኢንግሊዘኛ እና ስፓኒሽኛ]
- አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ፥ በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ስለ ውርስ ኑዛዜ ጠበቃ ላልሆኑ ሰዎች መመሪያ [ኢንግሊዘኛ እና ስፓኒሽኛ]
- ስለ ፍርድ ቤቶች የማህበረሰብ መመሪያ [ኢንግሊዘኛ እና ስፓኒሽኛ]
- የፈራዶ ተግባር: ለዜጎች ጠቃሚ መረጃዎች
- አስተያየት እና የቅሬታ መመሪያ

ኢሜይል info@courtexcellence.orgበመጠቀም የእነዚህን ህትመቶች የወረቀት ኮፒዎችን ይጠይቁ።

CCE የሚደጎመው በግለሰቦች፣ ኮርፖሬት፣ በተቋም፣ እና በሌሎች እርዳታ ሰጪ ልግስና ነው። ከታክስ የሚቀነስ ድጎማ ለማድረግ፣ እባክዎ እዚህ ይጎብኙ courtexcellence.org/get-involved/donate or call 202-785-5917.

The Council for Court Excellence is a 501(c)(3) nonprofit organization (ቲን: 52-1241825). ሕግ በሚፈቅደው መጠን ድረስ ልገሳዎች ከታክስ የሚቀነሱ ናቸው።

# ሠራተኞች እና ኤክዝኪዩቲቭ ኮሚቴ

**ዋና ሰብሳቢ**
**ሆነራሪ ሲቨን ኤሪክ ሆልምስ**
*ኬፒኤምጂ ኤልኤልፒ*

**ፕሬዚደንት**
**ኢርቪን ቢ ናታን**
*አርኖልድ ኤንድ ፖርተር ኤልኤልፒ (በሞት የተለየ)*

**የቅርብ ያለፈ ፕሬዝደንት**
**አርል ጀ ሲልበርት**
*ዲሌኤ ፓይፐር ኤልኤልፒ (ዩኤስ)*

**ምክትል ፕሬዝደንት**
**ጃክ ኢ. ስትራውስማን**
*ሲቪክ ዳይረክተር*

**ፀሀፊ**
**ላሪ ኢ. ሂንተን**
*ጂኮ*

**ትሬዥረር እና የገንዘብ ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ**
**ጁሊያ ኤ ማቲውስ**
*ሲቪክ ዳይረክተር*

**እጩ አቅራቢ ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ**
**ድዋይት ዲ. ሙራይ**
*ስቲን ሚቼል ሲፖሎኒ ቢያቶ እና ሚዝነር ኤልኤልፒ*

**ጀምስ ዲ ቤሪ ጅንየር**
*ሲቪክ ዳይረክተር*

**ካሮል ኤልደር ብሩስ**
*ኬ ኤንድ ኤል ኤልኤልፒ*

**ፓውሊት ኢ ቻፕማን**
*ኮንዝ መኪኒ ጀንሰን ዲዮፖሊስ እና ላይትፉት ኤልኤልፒ*

**ባሪ ኮበርን**
*ኮበርን እና ግሪንባውም ፒኤልኤልሲ*

**ዴቪድ ኤች ኮክስ**
*ጃክሰን ኤንድ ካምብል ፒሲ*

**ለስሊ ጊቫርዝ**
*ሲቪክ ዳይረክተር*

**ኤሪክ ኤስ ግሎቨር**
*ሲቪክ ዳይረክተር*

**ላውራ አር ሃንድማን**
*ዴቪስ ራይት ትሪማይን ኤልኤልፒ*

**ጀምስ ኤች ሁልሚ**
*አርንት ፎክስ ኤልኤልፒ*

**ሆነራሪ ክሬግ ኤስ ኢስኮይ**
*ሱፐረር ኮርት ኦፍ ዘ ዲስትሪክት ኮሎምቢያ*

**ጆን ቢ (ጂይ) ኬነዲ**
*ዘ ዋሽንግተን ፖስት*

**ፒተር አር ኮልከር**
*ዞከር ስፐፒደር ኤሌልፒ*

**ቪክቶር ኢ. ሎንግ**
*ሬጊን ዛምብሪ ሎንግ፣ ፒኤሌኤልሲ*

**ቤንጃሚን ጂ ራዚ**
*ኮቪክተን ኤንድ በርሊንግ ኤልኤልፒ*

**ብራይን ኤል ሸዋብ**
*ቬናብል ኤልኤልፒ*

**ኤልዛቤት ኤ ስኩሊ**
*ባከርሆስቴትለር*

**ስቲዋርት ኤች ቶምሰን**
*ኤቨርሼድስ ሰዘርላንድ (ዩኤስ) ኤልኤልፒ*

**ጀምስ ፒ ቱቲ**
*ሲቪክ ዳይረክተር*

**ናታሊ ኤስ ዋልከር**
*ዌብስተር እና ፍሬድሪክሰን፣ ፒኤልኤልሲ*

**ሲንቲያ ጂ ራይት**
*ሲቪክ ዳይረክተር*

## ሠራተኞች

**ሲንትያ ደብልዩ ሮዝበሪ**
*ኤክዝኪዩቲቭ ዳይረክተር*

**ጄፍ ካፐሊ**
*የቢሮ አስተዳዳሪ*

**ሳራ ሚድዌይ**
*ፖሊሲ አናሊስት*

**ቤን ሞሰር**
*የሪሰርች እና ፖሊሲ አናሊስት*

**ዳኒ ሪድ ዴቨሎፕመንት ኤንድ ኮሙኒኬሽንስ ዳይረክተር**

**ኢምሊ ታትሮ**
*ሲኒየር ፖሊሲ ካውንስል*

**ኮርት ፎር ኮርት ኤክሰለንስ**
1111 14th Street NW, Suite 500
Washington, DC 20005-5628
202.785.5917

courtexcellence.org
facebook.com/**courtexcellence**
twitter.com/**CCE_for_DC**
linkedin.com/**company/council-for-court-excellence**

ካውንስል ፎር ኮርት
ጀስትስ
ፍትህን ለማህበረሰቡ ማሻሻል